አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረምረቃ መርሃግብር

# የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ

/በክልል 14 በሚገኙ ስድስት ትምህርትቤቶች ተተኳሪነት/

ዘለዓለም ወዳጅ

ሰኔ 1993 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
# የድህረምረቃ መርሃግብር

## የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት
## ትግበራ ግምገማ
/በክልል 14 በሚገኙ ስድስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት/

በ

ዘለዓለም ወዳጅ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ADDIS ABABA UNIVERSITY

# የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ
/በክልል 14 በሚገኙ ስድስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት/

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረምረቃ መርሃግብር

ለአማርኛ ማስተማር/TEAM/ ኤም.ኤ.
ዲግሪ መርሃግብር በከፊል ማሟያነት የቀረበ
ጥናታዊ ጽሁፍ

ዘለዓለም ወዳጅ

ሰኔ 1993 ዓ.ም

# ምስጋና

እድሜና ጤንነትን እንዲሁም ብቃትን ሰጥቶ በነገር ሁሉ መከናወንን ለኔ ያደረገ አምላኬና አባቴ እግዚአብሔር ይባረክ!!

ከሁሉም አስቀድሜ ከቅድመ ምረቃ ትምህርቴ አንስቶ እስከ አሁን ድረስ ምሁራዊ እገዛቸውን ሲለግሱኝ ለቆዩ እንዲሁም ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳዘጋጅ በማማከርና በማረም ከጎኔ ላልተለዩት መምህሬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ከልብ የመነጨ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመቀጠልም ባሳለፍኳቸው የትምህርት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ ቁሳዊና ሞራላዊ ድጋፍ ላደረገልኝ ወንድሜ አሸናፊ በቀለ አሁኑም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

ከዚህም ሌላ ትምህቴን እንድከታተል ሁኔታዎችን ላመቻቸልኝ ለዲላ የመምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እንዲሁም ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረምረቃ ትምህርት ቤት፣ ላስተማሩኝ መምህራን እና ለጓደኞቼ በሙሉ ያለኝ ልባዊ ምስጋናና አክብሮት እጅግ ላቅ ያለ ነው።

ምስጋናዬንም የማጠቃልለው ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ በመተየብ ተገቢ መልክ ላስያዙት ለወይዘሮ ዘነበች ሽፈራው እና ለወይዘሮ አስራት ብርቃየሁ "ልባዊ ምስጋናዬ እነሆ!!" በማለት ነው።

አመሰግናለሁ!!

## ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| ምስጋና ........................................ | i |
| ማውጫ ........................................ | ii |
| የሰንጠረዥ ዝርዝር........................................ | iv |
| አጠቃሎ ........................................ | v |

**ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ**

| | |
|---|---|
| 1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ | 1 |
| 1.2. የጥናቱ አላማ........................................ | 5 |
| 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ | 6 |
| 1.4. የጥናቱ ገደብ ........................................ | 7 |
| 1.5. የምህጻረ ቃላት መፍቻና የስያሜ ቃላት ወይም ሐረጋት ብያኔ (Operational Definition)........................................ | 8 |

**ምዕራፍ ሁለት፡ ክለሳ ድርሳን**

| | |
|---|---|
| 2.1. የመርሀትምህርት ትግበራ እሳቤ........................................ | 9 |
| 2.2. የመርሀትምህርት ትግበራ ግምገማ እሳቤ........................................ | 14 |
| 2.3. በመርሀትምህርት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች..... | 19 |
| 2.3.1. የመርሀትምህርቱ አዘገጃጀት........................................ | 19 |
| 2.3.2. የመምህራኑ ሁኔታ........................................ | 20 |
| 2.3.3. የትምህርት ቤቱ ሁኔታ ........................................ | 24 |
| 2.3.4. የድጋፍ ሰጪ አካላት አስተዋፅኦ........................................ | 26 |

**ምዕራፍ ሦስት፡ የጥናቱ ዘዴ**

| | |
|---|---|
| 3.1. የጥናቱ ሞዴል........................................ | 29 |
| 3.2. የናሙና አመራረጥ ዘዴ........................................ | 32 |
| 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ........................................ | 33 |
| 3.3.1. የጽሑፍ መጠይቅ........................................ | 33 |
| 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ........................................ | 34 |
| 3.3.3. የችሎታ መለኪያ ፈተና........................................ | 36 |
| 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ........................................ | 37 |

## ምዕራፍ አራት: የመረጃ ትንተና


4.1. ስለመርሀትምሀርቱና ስለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ መምህራኑ ያላቸው አመለካከት ........................................ 40

4.2. የመምህራኑ የማስተማር ሂደት ........................................ 42

4.3. የትምሀርት ቤቶቹ አጠቃላይ ገጽታ እንዴትነት ........................................ 46

4.4. የተማሪዎቹ የፈተና ውጤት ........................................ 58

4.5. በመርሃትምሀርቱ ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ ተላውጠዎች (factors)... 63


## ምዕራፍ አምስት: ጭምቅ፣ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች


5.1. ጭምቅ (Summary) ........................................ 68

5.2. ማጠቃለያ ........................................ 71

5.3. የመፍትሄ ሀሳቦች (Recommendations) ........................................ 72

ዋቢ ጽሁፎች ........................................ 74

አባሪዎች ........................................ 82

አባሪ ሀ. ለመምህራኑ ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ 'ክፍል አንድ' የተገኘ መረጃ ........................................ 83

አባሪ ለ. ለመምህራን የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ........................................ 84

አባሪ ሐ. ለርዕሳነ መምህራን የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ ........................................ 94

አባሪ መ. ለክፍል ውስጥ ምልከታ የተዘጋጀ እርከናዊ ልኬት (Rating scale) ........................................ 98

አባሪ ሠ. እያንዳንዱ የትምሀርት ክፍል ምን ያህል ዝርዝር አላማዎችና ምን ያህል ይዘቶች እንዳሉት እንዲሁም ምን ያህል ክፍለ ጊዜ እንደተመደበለትና በፈተናው ውስጥም በየትኞቹ ተራቁጥሮች እንደተገለፀ የሚያሳይ ሰንጠረዥ ........................................ 99

አባሪ ረ. የችሎታ መለኪያ ፈተና ........................................ 100

አባሪ ሰ. የካይ-ስኩየር ($X^2$)' ስታትስቲካዊ ስሌት ........................................ 106

## የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ ገጽ

1. የመምህራኑ አመለካከት ከጾታ ረገድ ሲታይ .............................. 40
2. በአርከናዊ ልኬት የተገኘ የክፍል ውስጥ ምልከታ ውጤት................ 43
3. የትምህርት ቤቶቹ የመማሪያ ክፍል ውስጣዊ ገጽታ እንዴትነት.......... 46
4. ለመማር ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ መሳሪያዎች
   አቅርቦት ሁኔታ ......................................................... 47
5. የመርሃትምህርትና የመምህር መምሪያ አቅርቦት ሁኔታ ................. 49
6. የትምህርት ቤቶቹ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ለቋንቋው
   ትምህርት የሚያደርጉት የመርጃ መሳሪያዎች (teaching aids)
   አቅርቦት /ዝግጅት መጠን ................................................. 50
7. የመርሃትምህርቱን ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ በመምህራኑ መካከል
   የሚኖር የመረዳዳት ሁኔታ እና ከርዕሰ መምህር የሚደረግ
   ድጋፍ ......................................................................... 51
8. በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚስተዋል የክፍለ ጊዜ ምደባ፣
   የተማሪዎች ብዛት እና መምህራኑ ያለባቸው የስራ ጫና............... 53
9. የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ እና የመምህራኑ ሁኔታ ................ 55
10. የትምህርት ቤቶቹ አደረጃጀትና የማስተማር ስርዓቱ (system)
   ተፅእኖ ......................................................................... 57
11. ከተለያዩ የትምህርት ክፍሎች አንጻር ከማለፊያ ነጥብ በላይና
   በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች ............................................. 59
12. በተለያዩ ትምህርት ቤቶች (ዞኖች) ከሶስቱ የትምህርት ክፍሎች
   አኳያ ከማለፊያ ነጥብ በላይና በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች........... 61
13. ከመደበኛው የማለፊያ ነጥብ (50%) አኳያ፣ የወደቁና ያለፉ
   ተማሪዎች ብዛት ............................................................ 62
14. በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተላውጦዎች
   አማካይ (mean) ውጤት እና የተጽዕኖ ደረጃ (Rank)................ 64

# አጠቃሎ (Abstract)


የዚህ ጥናት አላማ በክልል 14 ተግባራዊ እየሆነ የሚገኘው የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ከአተገባበር (Implementation) አኳያ ምን ገጽታ እንዳለው መመርመር ወይም መፈተሽ፣ እንዲሁም በትግበራው ሂደት የሚታዩ ተላውጦዎችን (factors) መርምሮ ማሳየትና ከውጤታማነትም ረገድ እንዴትነቱን መጠቆም ነው::

ይህንንም አላማ ከግቡ የሚያደርስ መረጃ ለማግኘት ሶስት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች - የጽሁፍ መጠይቅ፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የችሎታ መለኪያ ፈተና - ተግባራዊ ተደርገዋል:: በመረጃ ምንጭነት የተወሰዱትም ሀያ መምህራን፣ ስድስት ርዕሳነ መምህራንና 216 ተማሪዎች ናቸው::

የጥናቱ አካባቢ ክልል 14 እንደመሆኑ በክልሉ የሚገኙ ስድስቱም ዞኖች በተተኳሪነት ተወስደዋል:: በክልሉም ከሚገኙ ስልሳ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስድስቱ ብቻ -ከእያንዳንዱ ዞን አንድ አንድ- በተራ የነሲብ ናሙና (simple random sampling) ተመርጠዋል:: በመረጃ ምንጭነት የተወሰዱትም አካላት ከነኚሁ ስድስት ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ናቸው::

የጥናቱ ውጤት እንደጠቆመውም የመርሃትምህርቱ ትግበራ የተሳካ አይደለም:: ማለትም በመርሃትምህርቱና በመምህር መምሪያው ላይ በእቅድ ደረጃ የሰፈሩት ሁኔታዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ተግባራዊ ሆነው የተገኙት 21.4 በመቶ በሆነ መጠን ብቻ ነው፤ ከትግበራው በኋላ ፈተናውን ያለፉ ወይም የማለፊያ ነጥብ (50%) እና ከዛ በላይ ያስመዘገቡ ተማሪዎች 44.9 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው:: ይህ ደግሞ አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ከትግበራው በኋላ የሚጠበቀውን እውቀት መጨበጥ አለመቻላቸውን ያሳያል::

ከዚህም ሌላ፣ አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ለመርሃትመህርቱ ቀና(አዎንታዊ) አመለካከት ወይም ዝንባሌ እንደሌላቸውና አብዛኛዎቹም (65 በመቶ) ቋንቋውን የሚያስተምሩት ያለፍላጎታቸው ተመድበው እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል:: በተጨማሪም የትምህርት ቤቶቹ የመማር ማስተማር ድባብ እና የመማሪያ ክፍሎች ገጽታ መርሃትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ ለመተግበር እምብዛም አመቺ አለመሆኑንና በትግበራውም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ ተላውጠዎች መኖራቸውን በጥናቱ መገንዘብ ተችሏል:: ከተላውጠዎቹም መካከል የተማሪዎች ቀደምት ችሎታ (Background knowledge) አናሳ መሆን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ብዛት፣ አዲሱን መርሃትምህርት አስመልክቶ ለመምህራን የተሰጠ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመኖር፣ በመምህራን ላይ የሚኖር የስራ ጫና፣ በመርሃትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእውቀት ደረጃ ጋር አለመመጣጠን (የትምህርቱ ክባድነት) እና ከተለያዩ አስተዳደራዊ ክፍሎች ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን ዋና ዋናዎቹ ሆነው ተገኝተዋል::

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

መርሃትምህርት (Syllabus) ለአንድ የትምህርት አይነት በየክፍል ደረጃው ተመጥነው የሚቀርቡ አጠቃላይና ዝርዝር አላማዎችን፣ ይዘቶችን፣ ክንዋኔዎችን (Activities)፣ የክፍለ ጊዜያት መጠንን፣ ይዘቱን ለማቅረብ አመቺ ሊሆኑ የሚችሉ ስልተትወራዎችን ወይም ስነዘዴዎችን (Methods)፣የመማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን ወይም መርጃ መሳሪያዎችን እና የመገምገሚያ ስልቶችን የሚጠቁም ወይም በዝርዝር የሚያስረዳ ሰነድ (Document) ነው/ Ur, 1998 176-177/:: ይህንን ሰነድ እንግሊዞች "መርሃትምህርት" ይበሉት እንጂ የአሜሪካ የስነአስተምህሮ ሊቃውንት "ስርአተትምህርት (Curriculum) በሚል ስያሜ ይጠሩታል/ UNESCO, 1978:12/::

መርሃትምህርት በሚዘጋጅበት ጊዜ የሀገሪቱን፣ የህብረተሰቡንና የተማሪዎችን ማህበረባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ እንዲሁም ፍላጎት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል/Yalden, 1987:85፣ Ornstein and Hunkin, 1998: 312-316፣ Shiundu and Omulands, 1992: 162-164/:: በተጨማሪም ግልጽ እና የማያሻማ በሆነ መልኩ መዘጋጀት እንዳለበትም ምሁራን /klein, 1981፣ Fullan and Pomfret, 1977/ ይገልጻሉ:: በዚህ ሁኔታ የተቀረጸ መርሃትምህርት ደግሞ - ከዝግጅት አንጻር - የተዋጣለት ነው ማለት ይቻላል::

ይሁን እንጂ አንድ መርሃትምህርት በአግባቡ ቢዘጋጅም በመማር ማስተማሩ ሂደት በተገቢ መልኩ በተግባር ካልተተረጎመ በመርሃትምህርቱ የተነደፉት አላማዎች ከግቡ

ሊደርሱ አይችሉም። ይህንንም በተግባር የመተርጎም ሂደት አዎንታዊነት ወይም አሉታዊነት ለማረጋገጥ የመርሃትምህርቱ የክፍል ውስጥ ትግበራ ሊገመገም እንደሚገባ አያሌ ምሁራን/ ለምሳሌ Tyler, 1974፣ Pratt, 1980፣ Shiundu and Omulando, 1992፣ Fullan and Pomfret, 1977፣ Stern, 1992፣ Sayler and et al, 1981/ ያስረዳሉ።

ምሁራኑ እንደሚጠቁሙት የትግበራ ግምገማ መርሃትምህርቱ በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመመርመርና በመፍትሄው ላይ ለመወሰን፣ የመርሃትምህርቱን ጠንካራና ደካማ ጎን ለማወቅ፣ የታለመውን አላማ ማስገኘት አለማስገኘቱን ለመገንዘብ፣ ብሎም መርሃትምህርቱን አሻሽሎ አሊያም ለውጦ ለማቅረብ ያግዛል።

እንደሚታወቀው በአገራችን በተነደፈው አዲስ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ መሰረት ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ ቀድሞ ከነበረው አካሄድ ለየት ባለ መልኩ የቋንቋ መርሃትህርቶች ተዘጋጅተዋል። ማለትም ለአፊፊት እና ለኢአፊፊት የሚያገለግሉ ሁለት አይነት መርሃትምህርቶች ለየክፍል ደረጃው ተቀርጸዋል። በመርሃትምህርቶቹም መሰረት እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍት ተዘጋጅቶና በመጻህፍቱና መርሃትምህርቶቹ መካከል ያለው ተጣጥሞሽና ግንኙነት በይዘት ትንተና ተገቢነቱ በሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ተ. ወይም ICDR/1998/ ተረጋግጦ የመማር ማስተማሩ ሂደት እየተካሄደ ይገኛል።

ይሁን እንጂ መርሃትምህርቶቹ ከተግባራዊነት አንጻር በእርግጥ ስኬታማ ሆነዋል ወይ የሚለው ጥያቄ ምላሽ ያገኘ አይመስልም። ለዚህም ጥቅምት 5 ቀን 1993 ዓ.ም. "በመማር ማስተማሩ ሂደት ዙሪያ አያሌ እንቅፋቶች እያጋጠሙ ነው።" "እንቅፋቶችን

ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ነው።" በሚሉ ርዕሶች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣው የመምህራንና የትምህርት ሚኒስቴር ባለስልጣናት አስተያየት ጥሩ ፍንጭ ሊሆነን ይችላል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አንድ መርሃትምህርት ጥሩ ውጤት አስገኝቷል ወይም አላስገኘም ብሎ ለመናገር የግድ የትግበራ ሂደቱ (Implementation Process) መገምገም ይኖርበታል። በዚህም መነሻነት የዚህ ጥናት ባለቤት በማዕከላዊ ደረጃ ለአፊፊት ተማሪዎች ተዘጋጅተው በክልል 14 ውስጥ እየተተገበሩ ከሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርቶች ውስጥ የ4ኛ ክፍልን የትግበራ እንዴትነት ለመገምገም መርጧል። 4ኛ ክፍል የተመረጠበትም ምክንያት ክፍሉ የመጀመሪያው እርከን (Cycle) መገባደጃ ከመሆኑም ባሻገር ከውጤታቸው አኳያ የመድገም አሊያም ወደሚቀጥለው ክፍል (5ኛ) የመሸጋገር ውሳኔ በተማሪዎች ላይ መስጠት የሚጀመርበት ክፍል በመሆኑ ነው/ በአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት ተማሪዎች ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ድረስ የምዘና (የፈተና) ውጤትን ባላማከለ መልኩ በቀጥታ ከክፍል ወደ ክፍል እንደሚሸጋገሩ (Direct Promotion) ልብ ይሏል/።

ይሄ ጥናት ይዞት በተነሳው ሃሳብ ዙሪያ ከዚህ ቀደም በተለያዩ አጥኚዎች/ Hailu Dink, 1991፡ Selomon Ariaya,2000/ የተካሄዱ ጥናቶች ቢኖሩም ከቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ የተከናወኑ የሚከተሉት ናቸው፡

- **Melese Bedane** /1992/

የዚህ ጥናት አላማ ከ9-12ኛ ክፍል ያሉትን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርቶች መርምሮ ያለባቸውን ችግሮች መጠቆምና የትግበራውንም እንዴትነት መፈተሽ ነው። የጥናቱም ውጤት፥ በዚህ ክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች የቋንቋውን

ክሂሎች በተገቢው መንገድ እንዳያዳብሩ እንቅፋት የሆነባቸው በዋነኛነት ደረጃ የመርሃትምህርቱ አዘገጃጀት መሆኑን ጠቁሟል:: በተጨማሪም ትግበራው የተዋጣለት አለመሆኑን አሳይቷል:: ከዚህም በመነሳት አጥኚው አዲስ መርሃትምህርት መዘጋጀት እንዳለበት አስተያየቱን ሰንዝሯል::

- **Dawit Mekonnen** /1999/

ይህ ጥናት የተካሄደው በምስራቅ ጎጃም አካባቢ በሚገኙ ስምንት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት ሲሆን አላማውም የሰባተኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋ መርሃትምህርት አተገባበር ምን እንደሚመስል መመርመርና የታዩ ችግሮችን መጠቆም ነው:: ውጤቱም፡ መርሃትምህርቱ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆኑን ማለትም አላማው ከግቡ አለመድረሱን ያሳያል:: ለትግበራውም ስኬታማ አለመሆን በዋና ዋና ችግርነት የተጠቆሙት የመምህራኑ ብቃት (ችሎታ) ማነስ እና የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች አቅርቦት ማነስ ናቸው::

- **ታደሰ ሲባሞ** /1992/

የጥናቱ ዋና አላማ "አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ የ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን (ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች) ተማሪዎች የተዘጋጀው መርሃትምህርት አፈጻጸም ምን መልክ እንዳለው መገምገም" እና በትግበራው ሂደት የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች መጠቆም ነው::

የጥናቱም ውጤት እንዳሳየው ትግበራው ውጤታማ ሆኖ አልተገኘም:: ማለትም በመርሃትምህርቱ የተነደፉት አላማዎች በአመርቂ ሁኔታ ከግቡ አልደረሱም:: ለዚህም ሁኔታ መንስኤዎቹ የመምህራኑ ብቃት ማነስ፡ መርሃትምህርቱ ከተማሪዎቹ ዳራ ጋር

አለመጣጣሙ፣ በቂ የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች አቅርቦት አለመኖሩ፣ ወዘተ ሆነው ተገኝተዋል።

እንግዲህ ይህ አሁን የተከናወነው ጥናት፣ የትኩረት አቅጣጫው በቋንቋ ትምህርት ላይ መሆኑና መሰረት ያደረገውም በትግበራ ግምገማ ላይ በመሆኑ እላይ ከቀረቡት ሶስት ጥናቶች ጋር አንድነት አለው ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ የጥናቱ ዋና ትኩረት አማርኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ለማስተማር በተዘጋጀው መርሃትምህርት ላይ መሆኑና የጥናቱ አካባቢም ክልል 14 መሆኑ ከበፊቶቹ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል።

## 1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አላማ፣ በክልል 14 ተግባራዊ እየሆነ የሚገኘው የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርት ከተግባራዊነት ወይም ከአተገባበር (Implementation) አኳያ ምን ገጽታ እንዳለው መመርመር ወይም መፈተሽ ይሆናል። በዚህም ውስጥ የተማሪዎቹን ሁኔታ፣ የመምህራኑን ሁኔታ እንዲሁም በትግበራው ሂደት የሚታዩ ሁኔታዎችን በመፈተሽ እንዴትነታቸውን ለማሳየት ጥረት ይደረጋል። በዚህ መነሻነትም፣ ለሚከተሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች በጥናቱ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ይሞከራል፣ ወይም ጥረት ይደረጋል።

1.2.1. ለክፍሉ ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ለመርሃትምህርቱና ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ ምን አይነት አመለካከት ወይም ዝንባሌ አላቸው?

1.2.2. መምህራኑ በመርሃትምህርቱ ወይም በመምህር መምሪያው ላይ የሰፈሩትን የመማር ማስተማር መርህ ትደም ተከተሎች (Instructional Guidelines) በክፍል ውስጥ በትክክል ተግባራዊ ያደርጋሉ?

1.2.3. የትምህርት ቤቶቹ አጠቃላይ ሁኔታ (የመማር ማስተማሩ ድባብ፣ የመማሪያ ክፍሎች ገጽታ፣ ወዘተ) መርምሃትምህርቱን በተገቢ መልኩ ለመተግበር ምን ያህል አመቺ ነው?

1.2.4. ከትግበራው በኋላ ተማሪዎቹ የሚጠበቀውን እውቀት መጨበጥ ችለዋል?

1.2.5. በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

## 1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

አያሌ ምሁራን/ Shiundu and Omulando, 1992:179, Pratt, 1980:343, Oliva, 1988:115፣ Fullan, 1992:37፣ Jacobson, 1989:134/ በስፋት እንደሚያስረዱት የመርሃትምህርት ትግበራን መገምገም በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያጋጥሙ ሁኔታዎችን ለማወቅ፣ የመርሃትምህርቱን ደካማና ጠንካራ ጎን ለመፈተሽ ብሎም መሻሻል ያለበትን ለማሻሻል አሊያም እንደገና ለማዘጋጀት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡

1.3.1. በትግበራው ሂደት ለሚታዩ ችግሮች መንስኤያቸው ምን እንደሆነ ለማመልከትና መፍትሄአቸውንም ለመፈለግ ይረዳል፡፡

1.3.2. ለወደፊቱ በክልሉም ሆነ በሌሎች ክልሎች ለሚደረገው የመርሃትምህርት ዝግጅት ወይም ማሻሻያ ሥራ፡ የሚመለከታቸው ክፍሎች ከዚህ ጥናት ውጤት በመነሳት ምን ሁኔታ ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ ትምህርታዊ ተሞክሮ ይሆናል፡፡

1.3.3. ጠቅለል ባለ መልኩ በአሁኑ ጊዜ አገራችን (በተለይ ክልል 14) ከመማር ማስተማር ሂደት አኳያ በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ ምሳሌአዊ መረጃ ሊሆን ይችላል፡፡

1.3.4. በሌላ አካባቢ ተመሣሣይ ጥናት ለማካሄድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች አጋዥነት ይኖረዋል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ገደብ

ይህ ጥናት በክልል 14 በሚገኙ 6 ዞኖች ውስጥ የሚከናወንና በዞኖቹ ውስጥ የሚገኙ የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ብቻ የሚያካትት ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል በተለያየ መልኩ እንደተገለጸውም ትኩረቱ በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርት ትግበራ ላይ የተወሠነ ነው፡፡

ጥናቱም በናሙናነት ያካተታቸው ስድስት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነሱም ከእያንዳንዱ ዞን አንድ አንድ በነሲብ ናሙና (Random) የተመረጡ ናቸው፡፡

## 1.5 <u>የምህጻረ ቃላት መፍቻና የስያሜ ቃላት ወይም ሐረጋት ብያኔ (Operational Definintion)</u>

1.5.1. UNESCO ( United Nations Educational Scientific and Cultural Organization)= በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት

1.5.2. ሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ተ. (ICDR: Institute of Curriculum Development and Research)= የሥርአተትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ተቋም

1.5.3. ት.መ.ማ.ማ.ድ. = የትምህርት መሳሪያዎች ማደራጃና ማከፋፈያ ድርጅት

1.5.4. <u>ነጻ ዝውውር (Direct or Free Promotion):</u> በአሁኑ ወቅት በአገራችን እየተካሄደ ያለና የፈተና (የምዘና) ውጤትን ባላማከለ ወይም ባላገናዘበ መልኩ ተማሪዎች ከክፍል ወደ ክፍል (ከ1ኛ እስከ 4ኛ) በቀጥታ እንዲያልፉ (እንዲዘዋወሩ) የሚደረግበት የዝውውሮሽ ሂደት ነው:: ለምሳሌ አንድ ተማሪ በሁሉም ትምህርት እጅግ ዝቅተኛ ውጤት ቢያመጣም እንኳን ወደሚቀጥለው ክፍል በቀጥታ ይዘዋወራል እንጂ ባለበት የክፍል ደረጃ ደግሞ አይማርም::

1.5.5. <u>አሀዳዊ ወይም ግለ መር(self-contained) የማስተማር ዘዴ</u>፡ አሁን በአገራችን እየተሰራበት ያለ ዘዴ ሲሆን ይህም አንድ መምህር በአንድ ክፍል የሚገኙ ተማሪዎችን ብቻ እንዲይዝና ሁሉንም የትምህርት አይነት ራሱ ብቻ እንዲያስተምር የሚያዝ ዘዴ ነው::

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የመርሃትምህርት ትግበራ እሳቤ

የመርሃትምህርት ትግበራ የሚለውን ጽንሰሀሳብ አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ የምንነት ብያኔዎች ሰጥተዋል፡፡ የተለያዩ ብያኔዎች ሲባል ግን በጽንሰሀሳብ ደረጃ የሚለያዩ ማለት አይደለም፣ ከአገላለጽ አኳያ እንጂ፡፡ ለምሳሌ Fullan እና Pomfret/1977:336/ ጽንሰሃሳቡን "በእቅድ ደረጃ የቀረበውን ወይም የተዘጋጀውን የትምህርት ይዘት በተግባራዊ ሂደት የመጠቀም ሁኔታ ነው፡፡ በማለት ይበይኑታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Nunan/1988:122/ "የመርሃትምህርት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በስራ ላይ የመዋል ሁኔታ ነው፡፡" በማለት ገልጿል፡፡ ከዚህም ሌላ Grotelueschen/ 1980:86/ የመርሃትምህርት ትግበራ ማለት የትምህርት ግቦችን (goals) እና እቅዶችን (designs) በስራ ላይ የማዋል ሂደት ወይም ወደተግባር የመለወጥ ሂደት ማለት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ይህንንም ሃሳብ ሌሎችም ምሁራን /Giroux and et al. 1981፡ Marsh, 1992 ፡ Evans, 1993፡ Pratt, 1980 ፡ Brown, 1994፡ Berman and McLaughlin, 1970 / ይስማሙበታል፡፡ በአጠቃላይ ብያኔዎቹ የሚያስተላልፉት መልዕክት ተመሳሳይ ሲሆን ይሄውም የመርሃትምህርት ትግበራ ማለት በዕቅድ ደረጃ የቀረበ መርሃትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በተግባራዊ ሁኔታ የሚከሰትበት ሂደት እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

የተለያዩ ምሁራን/ Fullan and Pomfret, 1977፡ Ornstein and Hunkins, 1988/ እንደሚያስረዱት የመርሃትምህርት ትግበራ በተማሪዎች ላይ የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ

ለማካሄድ የሰዎች (People)፣ የመሣሪያዎች(materials) እና የመርሃግብር (Porgramme) የተጣመረ አደረጃጀት እንደሚያስፈልግ ይገልጻል።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የመርሃትምህርት ዝግጅት በትግበራው ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። አሉታዊ ከሆነ መርሃትምህርቱ መሻሻሉ አሊያም መቀየሩና በአዲስ መልክ መዘጋጀቱ የግድ ነው። ከዚህም ሌላ በአንድ ወቅት ተገቢ የነበረ መርሃትምህርት በሌላ ወቅት ተገቢነቱን ሊያጣ ስለሚችልም፣ ለውጥ ማስፈለጉ አሁንም የግድ ነው. የማህበረሰብ ፍላጎትና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ከጊዜ አንጻር ተለዋዋጭ ነውና። ለዚህም ነው ስርአተትምህርት ወይም መርሃትምህርት ተለዋዋጭ ነው የሚባለው። በመሆኑም የሚሻሻለው ወይም በአዲስ መልክ የሚዘጋጀው መርሃትምህርት በትግበራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ቀድሞ ከነበረው በተለየ መልኩ መከናወኑ የግድ ይሆናል።

የመርሃትምህርት ለውጥ ተካሄደ ሲባል ደግሞ አብረው የሚለወጡ አምስት ዋና ዋና ነገሮች መኖራቸውን Fullan እና Pomfret/1977:361-365/ ያስረዳሉ። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡

1. የርዕሰ ጉዳይ ወይም የመሳሪያዎች ለውጥ (Changes in subject matter or materials)
2. የአደረጃጀት ለውጥ (Changes in organizational sturucture)
3. የሚና ወይም የባህሪ ለውጥ (Changes in role or behavior)
4. የእውቀትና የግንዛቤ ለውጥ/ Changes in knowledge and understanding)
5. የአመለካከት ለውጥ /Changes in value internalization)

የርዕስ ጉዳይ ወይም የመሳሪያዎች ለውጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚያግዙ ማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዲሁም ለተማሪዎቹ በሚቀርቡት የትምህርት ይዘቶች ላይ የሚደረገውን ለውጥ የሚመለከት ነው፡፡ የአደረጃጀት ለውጥ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎቹን የቡድን አቀነጃጀት፣ የመማሪያ ክፍሉን አደረጃጀት እንዲሁም የአዳዲስ መማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያዎችን አቅርቦት ያካትታል፡፡ የሚና ወይም የባህሪ ለውጥ በማስተማር ስነዘዴ ላይ፣ ስነዘዴውን ለማራመድ በሚመረጡ ተግባራት (Tasks) እና ክንዋኔዎች (Activities) ላይ፣ እንዲሁም በተማሪዎችና በመምህራን ሚና ላይ መታየት ያለበትን ለውጥ የሚያመለክት ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ የምናገኘው ደግሞ የዕውቀትና የግንዛቤ ለውጥ ነው፡፡ ይህም መምህራን ከአዲሱ መርሃትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ የሚኖራቸውን የአላማ፣ የርዕስ ጉዳይ (Subject matter)፣ የአተገባበር ቅደም ተከተል (Implementation Strategy) እና የሚና ግንኙነት (role relationship) ግንዛቤ ያመለክታል፡፡ በአምስተኛ ደረጃ የምናገኘውም የአመለካከት ለውጥ ሲሆን በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ የሚሳተፉት አካላት ለመርሃትምህርቱ ያላቸውን አመለካከትና አላማውን ለማስፈጸም የሚኖራቸውን ፈቃደኛነት የሚያመለክት ነው፡፡

በአጠቃላይ - እንደምሁራኑ ገለጻ - በአዲስ መልክ የተዘጋጀ መርሃትምህርት ወይም የትምህርት ፕሮግራም በስራ ላይ ሲውል (ሲተገበር) እላይ የተገለጹት አምስት ነገሮች ከአዲሱ መርሃትምህርት ጋር በተጣጣመ መልኩ መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ አለበለዚያ ትግበራው ስኬታማ ሊሆን አይችልም፡፡ ለምሳሌ መርሃትምህርቱ ተለውጦ መምህራኑ እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ግንዛቤ ካልጨበጡና የቀድሞ የማስተማር ስልታቸውን ለውጠው ከአዲሱ ጋር የሚጣጣም ስልት ካላዳበሩ የትግበራው ሂደት በተሳካ መልኩ ሊከናወን አይችልም፡፡ በተጨማሪም መምህራኑ ለአዲሱ መርሃትምህርት ጥሩ የሆነ ዝንባሌ (አመለካከት) ከሌላቸውና የተነደፉትን አላማዎች ለማስፈጸም ፈቃደኝነት ከሌላቸው በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ መከሰቱ አይቀሬ ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የመርሃትምህርት ትግበራን አስመልክቶ የተሰነዘሩትን ሀሳቦች ባጭሩ አጭምቆ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል:: መርሃትምህርት ዕቅድ ነው፣ ትግበራ ደግሞ ዕቅዱን ወደ ተጨባጭ ተግባር ለውጦ የማቅረብ ሂደት ነው:: ይህም የትግበራ ሂደት የሚከናወነው በትምህርት ቤት ውስጥ በሚካሄድ የመምህራን፣ የተማሪዎችና የመሳሪያዎች ትምህርታዊ ተራክቦ ይሆናል:: የትግበራው ሂደት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መርሃትምህርቱ ራሱ በተገቢው መንገድ ሲዘጋጅና በትግበራው ሂደት ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ ክፍሎችም ከመርሃትህርቱ ጋር ተጣጥሞሽ ያለው ግንኙነት ሲኖራቸው ነው::

## 2.2. የመርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ እሳቤ

መርሃትምህርት ከሁለት አቅጣጫ ሊገመገም ይችላል:: ይሄውም ከቅርፅ እና ከአተገባበር ረገድ ነው:: ከቅርጽ ረገድ የሚደረገው ግምገማ፣ "የመርሃትምህርት ግምገማ" ሲባል ከአተገባበር ረገድ የሚደረገው ደግሞ "የመርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ" ሊባል ይችላል:: እነኚህ ሁለት የግምገማ ጽንሰ ሀሳቦች ግልጽ የሆነ ልዩነት እንዳላቸውና በተናጠል ሊታዩ እንደሚችሉ Talmage እና Scriven በ'Ornstein እና Hunkns/1988:250 - 254/ ውስጥ ያስረዳሉ::

የመርሃትምህርት ግምገማ፣ ከተግባራዊና ከውጤታዊ ማንነቱ ውጪ በአንድ መርሃትምህርት ውስጣዊ ባህሪ ላይ የሚደረግ ግምገማ ነው:: ማለትም እቅዱ በተገቢ መንገድ ተዘጋጅቷል? ጥልቀቱና ስፋቱ ምን ያህል ነው? አቀነጃጀቱ ምን ይመስላል? ምሉዕነት አለው ወይ? በምን አይነት መንገድ መሻሻል ይችላል? ወቅታዊ ነው ወይ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ጠቃሚነቱን መርምሮ ውሳኔ ላይ የመድረስ ሂደት ነው /Posner, 1992: 223/::

የመርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ፡ በእቅድ ደረጃ የሰፈረው አላማ ወደ ተግባር መለወጡ ወይም አለመለወጡ እንዲሁም ውጤታማ መሆን ወይም አለመሆኑ የሚመረመርበት ነው። ማለትም በመርሃትምህርቱ ምን ታቀደ? የዕቅዱ ትግባራዊነት ምን ያህል ነው? የክፍል ውስጥ መስተጋብሩ ምን ይመስላል? በትግበራው ሂደት የሚታዩ ችግሮች ምንድን ናቸው? መፍትሄአቸውስ ምን ሊሆን ይችላል? ወዘተ በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ ምርምር በማካሄድ ምላሽ የሚሰጥበት ሂደት እንደሆነ ምሁራን /Oliva, 1988:463: Posner, 1992:237:Lewy,1977:70: Doll,1977:367: Ornstein and Hunkins, 1988:250-251/ያስረዳሉ።

የመርሃትምህርት ትግበራ ግምገማን አስመልክቶ ከሚሰነዘሩቸው ሃሳቦች ወይም ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር ምሁራንን በሁለት ጎራዎች ከፍፍሎ ማየት ይቻላል። ይሄውም ግማሾቹ ከትግበራው በኋላ በሚገኘው ውጤት ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በሂደቱ ማለትም በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ፡ ውጤት-ተኮር (Goal-Oriented) ሲባሉ ሁለተኛውን ሀሳብ የሚያራምዱ ደግሞ ሂደት ተኮር (process-oriented) በመባል ይታወቃሉ/Worthen and Saunders, 1987:62-71:Lang, 1974:22-23/።

በውጤት-ተኮር ጎራ ስር፡ Bloom/1956/: Krathwohl and Masia/ 1964/ : Cronbach/ 1963/ : Mager/ 1962/ :Popham እና Baker /1970/ እና Tyler/1949/ በዋና ዋና ምሳሌነት እንደሚጠቀሱ እነ 'Worthen' ይገልጻሉ። በተጨማሪም በሂደት ተኮር ጎራ ስር ከሚፈረጁት ምሁራን መካከል፡ Provus/ 1971/ : Yoloye/1978/ : MaCDonald/

የሂደት ተኮር ግምገማ አራማጅ ምሁራን "አዲስ ማዕበል ገምጋሚዎች/New-wave Evaluators)" በሚል ስያሜ በመጠራት/ Parsons. 176:126/ በአንድ ጎራ ይመደቡ እንጂ፣ ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር በመሀከላቸው የተወሰነ ልዩነት ይታያል። ይህም፣ ምሁራኑ በነደፏቸው የተለያዩ የግምገማ ሞዴሎች ውስጥ የሚንፀባረቅ ነው። ለምሳሌ Stake/1967/ እና Stuffelebeam/1973/ በመርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ ጊዜ የመማር ማስተማሩን ሂደትም ሆነ በተማሪዎች ላይ የሚታየውን ውጤት (out come) በአንድ ላይ አጣምሮ ማየት ያስፈልጋል የሚል ሀሳብ አላቸው። እንደ Rippey (በ'Bohla, 1979:18-19' ውስጥ ይመለከቷል)፣ Parlett እና Hamilton (በ'Stenhouse, 1975: 112-113' ውስጥ ይመለከቷል) እንዲሁም Scriven (በ' parsons, 1976:126' ውስጥ ይመለከቷል) ያሉት ምሁራን ደግሞ በመርሃትምህርት ትግበራ ላይ ግምገማ ለማካሄድ ለውጤቱ አንዳች ሳይጨነቁ ሂደቱን ብቻ ማየቱ (መፈተሹ) በቂ እንደሆነ ይናገራሉ።

በ'Stake/1967:523-540/ የተቀመረው ሞዴል፣ "ተጣጥሞሽ የግምገማ ሞዴል (Contenance Evaluation Model)" በመባል የሚታወቀው ሲሆን በሶስት አጠቃላይ ተላውጦዎች፣ (Variables) ላይ የሚያተኩር ነው። ተላውጦዎቹም ቅድመ-ሁኔታዎች (Antecedents)፣ የመማር ማስተማር መስተጋብሮች (Transactions) እና ውጤት (Outcome) ናቸው። ይኸ ሞዴል የመማር ማስተማሩን ሂደትም ሆነ በሂደቱ የተገኘውን ውጤት አጣምሮ በመፈተሽ የመርሃትምህርት ትግበራን ለመገምገም የሚያስችል ነው። ከዚሁ ጋር በተጣመረ መልኩ በ' Stuffelebeam /1973:22-23/ የተቀመረው ሞዴል ደግሞ ' CIPP ' እየተባለ የሚጠራው ሲሆን ይህም በውስጡ አራት ተላውጦዎችን - የመማሪያ/ማስተማሪያ አውድ (Context) ፣ ለተስተምህሮ የሚቀርቡ ግብአቶች (Inputs) ፣ የክፍል ውስጥ መስተጋብራዊ ሂደት (Process) እና በመጨረሻ የሚገኘው ውጤት (Product) በማካተት

አሻሻሉም ሆነ አዲስ ፈጥሮ መጠቀም እንደሚችል ሌሎች ምሁራን/ Sayler and et al. 1981:332-333፡ Oliva. 1988:160/ ያስረዳሉ።

## 2.3 በመርሃትምህርት ትግበራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች

በመርሃትምህርት ትግበራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ወይም ተላውጦዎች በርካታ ናቸው። የተለያዩ ምሁራን በዋና ዋና ተላውጦነት የሚጠቅሷቸውን እንደሚከተለው ማብራራት ይቻላል።

### 2.3.1. የመርሃትህርቱ አዘገጃጀት

መርሃትምህርት ሲዘጋጅ በቅድሚያ ትኩረት መስጠት ያለበት በተማሪዎቹ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ ነው። በመሆኑም አዘጋጆች መርሃትምህርት የሚያዘጋጁላቸውን ተማሪዎች የማንነት ደረጃ ጠንቅቀው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ምሁራን/ Fullan. 1991:19-27፡ Ornstein and Hunkins. 1998:292/ እንደሚገልጹት ብዙውን ጊዜ የመርሃትምህርት አዘጋጆች ስለተማሪዎች ማህበረባህላዊ ዳራ እንዲሁም የዕውቀት ደረጃ የሚኖራቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑና መርሃትህርቱን በጥንቃቄ ስለማያዘጋጁ ሁኔታው በትግበራው ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ Saunders እና Vulliamy/1983:335/ የመርሃትምህርት ትግበራን አስመልክቶ በታንዛንያና በኒውጊኒ ባካሄዱት ንጽጽራዊ ጥናት በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳደሩት ተላውጦዎች መካከል ዋንኛው አዘገጃጀቱ እንደሆነ ተረጋግጧል። በአገራችን የተካሄዱ ጥናቶች/Hailu Dinka. 1991፡Melese Bedanie. 1992፡

Selomon Ariaya. 2000/ እንደሚጠቁሙትም በትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደር ረገድ የመርሃትምህርቱ ባህሪ ወይም አዘገጃጀት ግንባር ቀደም ስፍራ ይይዛል::

አያሌ ምሁራን /Klein. 1981: 154-155:Fullan and Pomfret. 1977:368-371: Fullan.1991:66-88: Gross and et al. 1971:129-135/ እንደሚያስረዱት አንድ መርሃትምህርት በተገቢ መንገድ እንዲተገበር አላማዎቹ በግልጽነት እና ባልተወሳሰበ መልኩ መቀመጥ አለባቸው:: አለበለዚያ ግን በተጠቃሚዎቹ ላይ ግርታ ስለሚፈጥሩ እንዲሁም መምህራኑን ስለሚያደናግሩ ትግበራው ሳይሳካ ይቀራል:: በመሆኑም አዘጋጆቹ ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎቹ ግልጽ የሆነና በእኩል ደረጃ ሊያግባባ የሚችል አቅድ መንደፍ ይጠበቅባቸዋል:: ይህንንም ለማድረግ አዘጋጆችና መምህራን እርስ በእርስ በመጣመር የሃሳብ ልውውጥ ማድረግ እንዳለባቸው Yalden/1987:87/ ይመክራል::

በአጠቃላይ አንድ መርሃትምህርት በሚዘጋጅበት ጊዜ የተማሪዎችን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ካልተቀረጸ እንዲሁም ያካተታቸው አላማዎች ግልጽነት ከጎደላቸው በተጠቃሚዎች ላይ የመደናገር ስሜት ይፈጥራል:: ይሄ ደግሞ በትግበራውም ሆነ በመጨረሻ በሚጠበቀው ውጤት ላይ አሉታዊ የሆነ አንድምታ እንደሚኖረው እሙን ነው::

## 2.3.2. <u>የመምህራኑ ሁኔታ</u>

መርሃትምህርትን ወደ ተግባር ከመለወጥ አኳያ መምህራን ያላቸው ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው/ Saunders and Valliamy, 1983:361/:: ማለትም በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን የመማር ማስተማር ሂደት የሚመሩት - ተማሪዎችን ማደራጀት፡ የክፍልና የቤት ስራ መስጠት፡ መቆጣጠር፡ ተገቢ የሆነ ስነዘዴ መጠቀም፡ መርጃ መሳሪያዎች ማቅረብ፡

ምጋቢ ምላሽ መስጠት፣ ወዘተ መምህራን ናቸው። በመሆኑም፣ የመምህራኑ ሁኔታ ወይም ማንነት የትግበራውን ሂደት ሊያደናቅፈው አልያም ስኬታማ ሊያደርገው ይችላል።

'የመምህራኑ ሁኔታ' የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ በሁለት አቅጣጫዎች ከፍሎ ማየት ይቻላል። ይሄውም አንደኛ፣ መምህራኑ በመርሃትምህርቱ የሰፈሩትን ሀሳቦች ወደተግባር ለመለወጥ ያላቸው ብቃት ሲሆን ሁለተኛ፣ መርሃትምህርቱን ለመተግበር ያላቸው ዝንባሌ ወይም ስለመርሃትምህርቱ ያላቸው አመለካከት ይሆናል።

የተለያዩ ምሁራን/ Fullan, 1991:117-141፣ Clark and Peterson, 1986:256-257፣Ornstein and Hunkins, 1988:227፣ Sayler and et al, 1981:260/ እንደሚያስረዱት ምንም እንኳን አንድ መርሃትምህርት በጥራት ቢዘጋጅም መምህሩ እቅዱን ወደ ተግባር ለመለወጥ ያለው ብቃት ወይም ግንዛቤ ዝቅተኛ ከሆነ፣ የትግበራው ውጤት ሊደናቀፍ ይችላል። ምክንያቱም እነኚሁ ምሁራን እንደሚገልጹት ለመርሃትምህርት ትግበራ ዋንኛውና ውሳኙ ሰው መምህሩ በመሆኑ ነው።

Gross እና ተባባሪዎቹ/ 1971:123-135/ እንዲሁም Klein/1981:154-155/ እንደሚያስረዱትም የአንድ መርሃትምህርት ትግበራ እንዴትነት ስኬታማነት ወይም ድንቃፌ- መምህሩ ስለመርሃትምህርቱ ባለው ግንዛቤና ለመተግበር ባለው የብቃት ደረጃ ሊወሰን ይችላል። ማለትም መምህሩ ስለመርሃትህርቱ በቂ ግንዛቤ ከሌለው በመምሪያው (instructional plan) እና በመርሃትህርቱ ውስጥ የታለሙት ነገሮች ስኬታማ ሊሆኑ አይችሉም።

ይሄ ሁኔታ ደግሞ መርሃትምህርት በተቀየረ ወይም በተሻሻለ ጊዜ መምህራኑም የሙያ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል ወደሚል አስተሳሰብ ሊያመራን ይችላል። ምክንያቱም

ፍላጎት፣ የተሳትፎ ደረጃ (Level of commitment) እና ክሂል ከግምት ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው የሚመክሩት።

Langenbach/1972:35-38/ ያካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው መምህራን ለትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ዝንባሌና ቀና አመለካከት ለማሳደግ በመርሃትምህርቱ ቀረጻ ላይ መምህራኑን ማሳተፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ምሁሩ ባካሄደው ጥናት በመርሃትምህርት ቀረጻ ወቅት ተሳታፊ የነበሩ መምህራን ካልተሳተፉት ይልቅ ለመርሃትምህርቱ ቀና አመለካከት እንዳላቸውና ለትግበራውም ጥሩ ተነሳሽነት እንደሚያሳዩ ተረጋግጧል።

በመርሃትምህርት ዝግጅት ላይ መምህራንን ማሳተፍ መምህራኑ ለትግበራው የሚኖራቸውን ዝንባሌና ቀና አመለካከት ከማሳደጉም በተጨማሪ ለአዲሱ መርሃትህርት የሚኖራቸው የአተገባበር ግንዛቤ እንዲጨምርና ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ለማካሄድ እንደሚረዳ ምሁራን/ Gross and et al.1971:25፣ McNeil.1990:227-228/ ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ የመምህራኑ ሁኔታ-ብቃት እና ዝንባሌ- በመርሃትምህርት ትግበራ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። በመሆኑም እላይ እንደተመለከትነው የመምህራኑን ብቃት ወይም ለአዲሱ መርሃትምህርት የሚኖራቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፣ ለትግበራው እንዲሁም ለመርሃትምህርቱ ለራሱ የሚኖራቸውን ዝንባሌና ተነሳሽነት ለማሳደግ ደግሞ በዝግጅቱ ወቅት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ጠቃሚ ነው። በዝግጅቱ ውስጥ መሳተፍ ሲባል ግን እያንዳንዱ መምህር መደበኛ ስራውን ጥሎ በቀረጻ ሂደት ውስጥ ይገባል ማለት ላይሆን ይችላል፣ በተለያዩ መንገዶች

አስተያየቶችንና ግንቢ የሆኑ ተሞክሯዊ ሀሳቦችን በመሰንዘር ለዝግጅቱ አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለት ነው እንጂ::

### 2.3.3. <u>የትምህርት ቤቱ ሁኔታ</u>

መርሃትምህርት ተግባራዊ የሚደረግበት ዋንኛ ስፍራ ትምህርት ቤት ነው:: በመሆኑም የትምህርት ቤቱ ሁኔታ የትግበራውን ሂደት ስኬታማ ሊያደርገው አሊያም ሊያደናቅፈው ይችላል:: ማለትም የትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ድባብ የክፍሉ ሁኔታ፣ የመርጃ መሳሪያዎች መገኘት፣ የተለያዩ የመማሪ ማስተማሪያ ቁሳቁስ በበቂ ሁኔታ መኖር፣ ወዘተ- በመርሃትምህርቱ ውስጥ በዕቅድ ደረጃ የሰፈሩትን ክንውኖች (ተግባሮች) በተግባር ለማካሄድ አመቺ ከሆነ በትግበራው ውጤት ላይ አዎንታዊ አንድምታ ይኖረዋል፣ አለበለዚያ ግን ራሱን የቻለ መሰናክል መሆኑ አይቀርም::

ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ በተለያዩ ታዳጊ አገሮች (ቡሩንዲ፣ ህንድ፣ የመን፣ ሞዛምቢክ እና ካሜሩን) በተካሄደ ጥናት ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁስ (ጠረጴዛ፣ወንበር፣ዴስክ፣ስሌዳ) እና የመርጃ ማሳሪያዎች እጥረት እንዳለና ይህም በመርሃትምህርት ትግበራ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ እንደሚገኝ ምሁራን/Caillods and Postlethwaite, 1989:172-173/ ይጠቁማሉ:: በተመሳሳይ መልኩ Ross እና Postlethwaite/1992:28/ እንደገለጹት በዚምባቡዌ በተደረገው ጥናት ለጥናቱ ከተመረጡት ናሙና ትምህርትቤቶች/1ኛ ደረጃ/ ውስጥ አስሩ ጥቁር ሰሌዳ የላቸውም፣ በቂ የመቀመጫ ስፍራ ያላቸው 18.4 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው፣ ተማሪዎች ተስፋፍተው እንዲጽፉ በቂ የመጻፊያ ስፍራ ያላቸው ደግሞ 11.5 በመቶዎቹ ብቻ ሆነው ተገኝተዋል::

## 2.3.4. የድጋፍ ሰጪ አካላት አስተዋጽኦ

የመርሃትምህርት ትግበራ የብዙ ሰዎችና የሚመለከታቸው አካላት ጥምር ሂደት ነው:: ማለትም ውጤታማ የሆነ ትግበራ ለማካሄድ የአዘጋጆቹ፣ የቢሮ ሃላፊዎች፣ የትምህርት ባለሙያዎች፣ የኢንስፔክተሮች፣ የርዕሳነ መምህራን፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ሠራተኞችና የመምህራን ቅንጅታዊ ስራ ያስፈልጋል:: Ornstein እና Hunkins/1988:228/ እንደሚያስረዱት ለትግበራ ስኬታማነት ከመምህራን ጋር ቅንጅታዊ ስራ ከማካሄድ ረገድ ግንባር ቀደሙን ስፍራ መያዝ ያለባቸው የመርሃትምህርቱ አዘጋጆች መሆን አለባቸው:: ቅንጅቱንም መፍጠር የሚቻለው አዲስ የትምህርት ፕሮግራም በሚዘጋጅበት ጊዜ አዘጋጆቹ የተለያዩ አውደጥናቶችና የውይይት መድረኮች በመፍጠር መምህራኑንና የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማሳተፍ ነው:: ይህንንም ሀሳብ Stern /1992:46/ እና Zeltman እና ተባባሪዎቹ /Fullan and Pomfret, 1977:374 ውስጥ ይመለከቷል/ ይስማሙበታል::

ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ የመርሃትህርት አዘጋጆች ለዝግጅቱ እንጂ ለትግበራው ትኩረት ሲሰጡ አይታይም:: ማለትም መምህራን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ምሁራዊ እገዛ ከማድረግ ወይም እንዴት እንደሚተገብሩ በመገምገም ችግሮችን ለማቃለል ጥረት ከማድረግ ሲታቀቡ ይስተዋላል:: ይህ ደግሞ ምንም እንኳን መርሃትምህርቱ ከዝግጅት ረገድ የተዋጣልት ቢሆንም ከትግበራ አንጻር ውጤት አልባ እንዲሆን ያደርገዋል/Pratt, 1980:409-426/::

Hawes /1979:179-180/ እና Gross እና ተባባሪዎቹ /1971:200-201/ እንደሚገልጹት ለአንድ መርሃትምህርት ትግበራ ስኬታማነት የትምህርት ቤት

ተቆጣጣሪዎች፣ የትምህርት ቢሮ ሀላፊዎች፣ የስነአስተምህሮ ጠበብት እና ርዕሳነ መምህራን ቋሚ ንቁ የሆነ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ሌሎች የመስኩ ምሁራን/Ornstein and Hunkins, 1998:228-243፣ Fullan, 1991፣ 143፣ Snyder and et al 1996፣ 417/ ደግሞ ምንም እንኳን እላይ የተዘረዘሩት አካላት አስፈላጊ ቢሆኑም ለትግበራው ስኬታማነት ርዕሳነ መምህራን በዋናነት መጠቀስ እንዳለባቸው ይናገራሉ። ምክንያቱም ርዕሳነመምህራን ከመምህሩ እኩል ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ አውድ ቀረቤታ ስላላቸው ነው።

ከዚህም ሌላ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ሰራተኞች ወይም የመማሪያ ማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ባለሙያዎች ለመርሃትምህርት ትግበራ ስኬታማነት ጥረት ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ምሁራን/Sampath and et al. 1984:70/ ያስረዳሉ።

ጠቅለል ባለ መልኩ ምሁራን ከሰነዘሯቸው ሀሳቦች በመነሳት የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ አካላት- ቀደም ሲል የተዘረዘሩት-የመርሃትምህርቱን ትግበራ ስኬታማ የሚያደርጉት በምን መንገድ እንደሆነ እንደሚከተለው አጫምቆ ማቅረብ ይቻላል፣

- ከተዘጋጀው መርሃትምህርት ረገድ የመምህራኑ ሚና ምን መሆን እንዳለበት ግልጽ የሆነ እይታ መስጠት፣
- ተገቢ የሆነ የመማር ማስተማር መዋቅራዊ ቅንጅት በትምህርት ቤት ውስጥ መፍጠር፣
- መርሃትምህርቱን በተገቢው መልኩ ለመተግበር እንዲችሉ አስፈላጊ የሆኑ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን ለመምህራን መስጠት፣
- መምህራኑን ለትግበራው ለማነሳሳት የተለያዩ ማበረታቻዎችን መስጠት፣
- ለመርሃትምህርቱ ትግበራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ማቅረብ፣

- የመምህራኑን የማስተማር ሂደት በመገምገም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት በጋራ ጥረት ማድረግ፡፡

እንግዲህ እላይ እንደተገጸው ድጋፍ ሰጪ አካላት ከመምህራኑ ጋር በመቀናጀት ለትግበራው ሂደት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ካላደረጉ የመርሃትምህርት ትግበራ ስኬታማነት በመምህራን ጥረት ብቻ ላይገኝ ይችላል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በታዳጊ አገሮች ውስጥ የመርሃትምህርትን ትግበራ ስኬታማነት ከሚያስተጓጉሉ ተላውጦዎች መካከል ይህ የትንጅታዊ ስራ ጥረት አለመኖር መሆኑንም ምሁራን/ Caillods and Postlethwaite, 1989:172/ ይጠቁማሉ፡፡

በአጠቃላይ በስፋት እንደተመለከትነው የአንድን መርሃትምህርት ትግበራ ውጤታማነት ወይም ድንቃሬ የሚወስኑ አያሌ ተላውጦዎች አሉ፡፡ ተላውጦዎቹም እላይ በዝርዝር በተገለጹት ዋና ዋና ሁኔታዎች -የመርሃትምህርቱ አዘገጃጀት፣ የመምህራኑ ሁኔታ፣ የትምህርት ቤቱ ሁኔታ እና የድጋፍ ሰጪ አካላት አስተዋጽኦ- ስር ተጠቃለው እንደሚቀርቡ ልብ ይሏል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ዘዴ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት አላማ በክልል 14 ውስጥ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርት አተገባበር እንዴትነትን መገምገምና በትግበራ ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉትን ችግሮች ማሳየት ብሎም መፍትሄ ሃሣብ መጠቆም ነው። እናም ጥናቱ ገላጭ ቅኝት (Descriptive Survey Method) የጥናት ዘዴ ይጠቀማል።

### 3.1 የጥናቱ ሞዴል

ይህንን ጥናት ለማካሄድ የተመረጠው ሞዴል "Congruence Contingency Model" የተሰኘው ሲሆን ይህም Stake/1967/ የቀመረው ነው። ይህ ሞዴል አብዛኛውንም ጊዜ "Stake Model" በመባል ይታወቃል።

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ እንደተገለጸው ይህ ሞዴል የመማር ማስተማር ሒደትንም ሆነ የተስተምህሮውን ውጤት በማጣመር የትግበራ ግምገማ ለማካሄድ የሚያግዝ ነው። ከዚህም ሌላ በውስጡ ሶስት ተላውጦዎችን አካቶ ይዟል። እነሱም ቅድመ ሁኔታዎች (Antecedents)፣ የመማር ማስተማር መስተጋብሮች (Transactions) እና የተስተምህሮ ውጤቶች (Outcomes) ናቸው።

ቅድመ ሁኔታዎች የሚባሉት ከመማር ማስተማሩ ሂደት በፊት የሚገኙና ከሂደቱ በኋላ በሚጠበቀው ውጤት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ናቸው። ከዚህ ጥናት አኳያ የተማሪዎቹ ቀደምት እውቀት (Background knowledge)፣ የመምህራኑ አመለካከት የትምህርት ቤቶች ሁኔታ እና የድጋፍ ሰጪ አካላት

አስተዋጽኦ በቅድመ ሁኔታነት (Antecedents) ተወስደዋል። ተራክቧዊ ሂደቶች ወይም የመማር ማስተማር መስተጋብሮች (Transaction) ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪ ከተማሪ፣ ተማሪ ከመምህር፣ ተማሪ ከመጻህፍት፣ ወዘተ ጋር የሚደረጉትን ግንኙነቶች የሚያካትቱ ተላውጦዎች (variables) ናቸው። ከዚህም ሌላ መምህራኑ በመርሃትምህርቱ ውስጥ በንድፍ ደረጃ የተገለጹትን የትምህርት ይዘቶች በተገቢው መልኩ በተግባር የመተርጎም ብቃትም በተራክቧዊ ሂደቶች ውስጥ ሊካተት የሚችል ነገር ይሆናል። እነኚህ ተላውጦዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄደው ምልከታ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቅ እንዴትነታቸው ወይም ምንነታቸው የሚረጋገጥ ነው። በመጨረሻም የተስተምህሮ ውጤቶች የሚባሉት በመማር ማስተማሩ ሂደት የተነሳ በተማሪዎቹ ላይ ሊታዩ የሚችሉት የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጦች ናቸው። ከዚህ ጥናት አኳያ ተማሪዎች በመርሃትህርቱ ውስጥ የሰፈሩትን የትምህርት ይዘቶች በተገቢ መልኩ መጨበጥ መቻላቸውን ለመረዳት በተዘጋጀው ፈተና አማኝነት የሚገኘው መረጃ በተስተምህሮ ውጤትነት (outcome) ይወሰዳል።

በአጭሩ የዚህን ሞዴል አጠቃላይ ምንነት ወይም እንዴትነት ከሚከተለው ቻርት በግልጽ መረዳት ይቻላል።



ከቻርቱ እንደምንገነዘበው በእቅድ ደረጃና በተግባራዊነት የተቀመጡ ተላውጦዎች (Variables) አሉ፡፡ የሞዴሉም አካሄድ በእቅዱና በተግባራዊ እይታው መካከል ተጣጥሞሽ አለ ወይስ የለም ለሚለው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ማስገኘት ነው፡፡

እቅድ (intent) - ከዚህ ጥናት አኳያ የሚለው ጽንሰሀሳብ የሚያመለክተው በአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ምርሃትምህርትና በመምህሩ መምሪያ ላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች ይሆናል፡፡ ተግባራዊ እይታ (Observation) ደግሞ መርሃትምህርቱ በሚተገበርበት ጊዜ በመስክ ጥናት የሚገኘው ተጨባጭ መረጃ ነው፡፡ የዚህም ጥናት አላማ በእቅዱና በተግባራዊው ሂደት መካከል ተጣጥሞሽ መኖር ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ በመሆኑ "Stake Model" ለጥናቱ አመቺ ሞዴል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በርካታ ምሁራን/ ለምሳሌ Posner. 1992:237-238፣ Sayler and et al, 1981:356፣ Ornstin and Hunkins, 1988:259-260/ እንደሚያስረዱት "ስቴክ ሞዴል" ከሌሎች ሞዴሎች ይልቅ አመቺ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክንያቱም ሌሎች የግምገማ ሞዴሎች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ብቻ አሊያም በውጤት ላይ ብቻ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡ ይህኛው ሞዴል ግን ሂደቱንም ሆነ ውጤቱን በአንድነት አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ይህ ሞዴል የመማር ማስተማሩን ሂደት በተለይም በክፍል ውስጥ የሚካሄድን እንቅስቃሴ ለመገምገም እጅግ ጠቃሚ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂደታዊም (Formative) ሆነ ፍጻሜአዊ (Summative) ግምገማ ለማካሄድ እንደሚረዳ ምሁራን/ MaCormic and James, 1989:179/ ያስረዳሉ፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ይኼ ጥናት የሚያካትተው በክልል 14 ውስጥ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶችን ነው። ከክልሉ ትምህርት ቢሮ በተገኘው መረጃ መሰረት፡ በስድስቱ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ የመንግስት ትምህርት ቤቶች 62 ናቸው። ከእነኚህም አንዱ በ1990 ዓ.ም የተቋቋመ በመሆኑና 4ኛ ክፍል ማስተማር ያልጀመረ በመሆኑ ከጥናቱ ተተኳሪነት ተወግዷል። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዓላማ የአራተኛ ክፍልን አማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራን መገምገም በመሆኑ ነው።

የቀሩትን 61 ትምህርትቤቶችም ከጊዜ እጥረት፥ ከገንዘብ አቅምና ከጉልበት ውስንነት የተነሳ በሙሉ ማካተት ስለማይቻል ከእያንዳንዱ ዞን አንድ አንድ በድምሩ 6 ትምህርትቤቶች ብቻ በሎቶሪ ዘዴ በናሙናነት ተመርጠዋል።

በናሙናነት ከተመረጡት 6 ትምህርትቤቶች ውስጥ በተራ የነሲብ ናሙና (Simple Random' Sampling) ከእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ክፍል (4ኛ ክፍል) ተወስዷል። በናሙናነት በተወሰዱት ክፍሎች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን የማስተማር ሂደትም በምልከታ ተገምግሟል። ከዚህም ሌላ በናሙናነት በተመረጡት ትምህርትቤቶች ውስጥ የሚገኙ 6 ርዕሳን መምህራንና 20 የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አስተማሪዎች በመረጃ ምንጭነት ተወስደዋል። ማለትም የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል።

በተጨማሪም ከስድስቱ ትምህርትቤቶች ውስጥ ከእያንዳንዳቸው 36፡ በአጠቃላይም 216 ተማሪዎች ችሎታ መለኪያ ፈተና ( Achievement test) እንዲወስዱ ተደርጓል።

የተማሪዎቹም አመራረጥ ስስቱንም የችሎታ ደረጃ ( Academic Performance) - ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ - ባማከለ መልኩ የተከናወነ ነው።

### 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል። እነሱም የጽሁፍ መጠይቅ (Questionnaire)፣ የክፍል ውስጥ ምልከታ (Classroom observation) እና ችሎታ መለኪያ ፈተና (Achievement Test) ናቸው።

#### 3.3.1. የጽሁፍ መጠይቅ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የጽሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀው ለመምህራንና ለርዕሳነ መምህራን ነው። ለመምህራኑ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ አምስት ክፍሎች ያሉት እና በዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት የሚያገለግል ሲሆን ለርዕሳነ መምህራን የተዘጋጀው ደግሞ በመምህራኑ ምላሽ ላይ በአጋዥነት የሚያገለግል ነው/ አባሪ ለ እና አባሪ ሐ ይመልከቱ/።

የጽሁፍ መጠይቆቹ ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት በምሁራን ተገምግመዋል። እንዲሁም የእያንዳንዱ ጥያቄ አስተማማኝነት (Reliability) እና የመለየት አቅም (Discrimination power) አስቀድሞ በቅኝት ጥናት (Pilot Study) አማካኝነት ለመፈተሽ ተሞክሮ አስፈላጊ የማስተካከያ ሥራ ተካሂዷል።

ምሁራን /ለምሳሌ Burrough, 1975: 120/ እንደሚያስረዱት አመለካከትን የሚጠይቁ ዐረፍተነገሮች (statements) የመለየት አቅም በቀመር ሲሰላ የሚገኘው ውጤት ከ0.5 በታች መሆን የለበትም:: ማለትም የስሌቱ ውጤት ከ0.5 በታች ከሆነ ጥያቄዎቹ (Statements) ተገቢ የሆነ የመለየት አቅም የላቸውም ማለት ነው:: ይህ ከሆነ ደግሞ ጥያቄዎቹ ተቀባይነት አይኖራቸውም::

ከቅኝት ጥናቱም በመነሳት የመምህራንን አመለካከት የሚፈትሹና የመለየት አቅማቸው ከ0.5 በላይ የሆነ 12 አረፍተነገሮች በዋናው ጥናት ውስጥ ተካተዋል/ አባሪ ለ ክፍል ሁለት'ን ይመለከቷል/:: የነኚህም አረፍተነገሮች ልኬ-ተዛምዶ (Consistancy Coefficient) በ 'Split-half reliability method' ሲሰላ ውጤቱ 0.93 ሆኖ ተገኝቷል:: ይህም፣ አረፍተነገሮቹ አግባብነት ያለው ውስጣዊ ዝምድና (good internal consistancy of the items) እንዳላቸው ያረጋግጣል::

ሌሎቹም ጥያቄዎች ተገቢ እንደሆኑና የታቀዱባቸውን አላማዎች ከግቡ የሚያደርሱ መሆናቸው በቅኝት ጥናቱ ተፈትሾ አንዳንድ ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ ለዋናው ጥናት እንዲውሉ ተደርገዋል::

### 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ

ምሁራን /Richards and Nunan, 1990:44፣ Wallace, 1991:76/ እንደሚያስረዱት ሁለት አይነት የምልከታ ስልቶች አሉ:: እነሱም ገደብ የለሽ የምልከታ ስልት (Ethinographic) እና ውስን (Fixed) የምልከታ ስልት ናቸው::

ልኬቱን (Rating scale) ተገቢነት ወይም ውጤታማነት ለማረጋገጥ ተችሏል። (በእርከናዊ ልኬት አማካኝነት ምልከታ ተካሂዶ በተመልካቾች መካከል የሚታየው የስምምነት ደረጃ ወደ 100% መጠጋቱ የእርከናዊ ልኬቱን ተገቢነት እንደሚያስረዳ ልብ ይሏል።)

### 3.3.3 <u>የችሎታ መለኪያ ፈተና</u>

የተለያዩ ምሁራን /Ornstein and Hunkins, 1988:250-251፥ Lewy, 1977:70/ እንደሚገልጹት የችሎታ መለኪያ ፈተና ከመማር ማስተማር ሂደት ወይም ከመርሃትምህርቱ ትግበራ በኋላ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት አለማምጣታቸውን ለመገምገም ወይም ለማረጋገጥ የሚያግዝ ዋንኛ መሳሪያ ነው። በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል።

ፈተናው የተዘጋጀው መርሃትምህርቱንና የተማሪውን መጽሀፍ መሰረት ተደርጎ ሲሆን የመጀመሪያውን መንፈቀ አመት ትምህርት ብቻ ያጠቃላሉ 42 ጥያቄዎች አካቶ ይዟል/አባሪ 'ረ' ን ይመለከቷል/። የፈተናውንም ተገቢነት (validity) ለማረጋገጥ በተለያዩ የመስኩ ባለሙያዎች ተገምግሞ አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎበታል።

ከዚህም ሌላ በሁለት ትምህርትቤቶችና በ60 ተማሪዎች ላይ በተካሄደው የቅኝት ጥናት የፈተናው የቅለትና የክብደት መጠን (Difficulty level) እንዲሁም የእያንዳንዱ ጥያቄ የመለየት አቅም ተተንትኖ ተገቢነቱን ለመመዘን ጥረት ተደርጓል። Madsen/1983:181-183/ እንደሚጠቁመውም አንድ ጥያቄ ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑ ተማሪዎች ከመለሱት በጣም ቀላል ነው፥ ከስላሳ በመቶ በታች የሚሆኑ ተማሪዎች ብቻ ከመለሱት ደግሞ በጣም ከባድ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህም ሌላ አስር በመቶና ከዛ በታች የመለየት አቅም ያለው ከሆነ ተቀባይነት የለውም፣ የመለየት አቅሙ አስራአምስት በመቶና ከዚያ በላይ ከሆነ ግን ተቀባይነት ይኖረዋል። ከዚህ አኳያ የፈተናው (ለዚህ ጥናት የተዘጋጀው) የቅለትና የክብደት መጠን በአማካይ 56.88 በመቶ በመሆኑና የመለየት አቅሙም በአማካይ 30.63 ሆኖ በመገኘቱ፣ ተቀባይነት ወይም ተገቢነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል።

በተጨማሪም 'kuder-Richardson Formula 21' የተሰኘውን ቀመር በመጠቀም የፈተናውን አስተማማኝነት (Reliability) ለመፈተሽ ተሞክሮ በቅኝት ጥናቱ የተገኘው ቀመራዊ ውጤት 0.62 ሆኖ ተገኝቷል። ይህም ውጤት የፈተናውን አስተማማኝነት የሚያሳይ ነው።

ፈተናው በዚህ ሁኔታ ተገቢነቱና አስተማማኝነቱ ተገምግሞ ለዋናው ጥናት ተግባራዊ ሆኗል። ማለትም በናሙናነት በተመረጡት 6 ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች 216 (ከእያንዳንዱ ትምህርትቤት 36 ተማሪዎች) ተመርጠው ፈተናውን እንዲወስዱ ተደርጓል። የፈተናውም አሰጣጥ በሁለት ክፍለ ጊዜ የተከፈለ ነው። ማለት፣ በ'ሀ' ስር የቀረቡት 5 ጥያቄዎችና በ'ለ' ስር ያሉ የመጀመሪያዎቹ 12 ጥያቄዎች በአንድ ክፍለ ጊዜ የተሰጡ ሲሆን፣ ከተራ ቁጥር 13 እስከ መጨረሻ ያሉት ደግሞ በሌላ ክፍለ ጊዜ ተሰጥተዋል። ይህም የተደረገው በተማሪዎች ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የመሰልቸት መንፈስ ለማስወገድ ነው።

### 3.4. <u>የመረጃ አተናተን ዘዴ</u>

ይህ ጥናት ምላሽ ሊፈልግላቸው ካነሳቸው ጥያቄዎች ሁኔታ አኳያ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (የጽሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታ፣ ፈተና) ተግባራዊ ሆነዋል። የተገኙትንም መረጃዎች ለመተንተን የተለያዩ ቴክኒኮች እጥቅም ላይ ውለዋል።

የመጀመሪያው የምርምር ጥያቄ ከአመለካከት ወይም ከዝንባሌ ጋር የተዛመደ በመሆኑ የመምህራኑን ምላሽ ለማግኘት የ'Likart Scaling Technique' ተግባራዊ ተደርጓል /አባሪ ለ ክፍል ሁለትን ይመለከቷል/:: መረጃውም የተተነተነው መምህራኑ እያንዳንዳቸው ካስመዘገቧቸው የምርጫ ድምር ውጤቶች አማካዩን (mean) በማስላትና ከአማካዩም አንጻር በከፍተኛና በዝቅተኛ ውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት በ 'chi-squar($x^2$)' እና በመቶኛ ስሌት በማነጻጸር ነው::

በዚህም መሰረት ከአማካዩ በላይ የተመዘገቡ ውጤቶች መርሃትምህርቱን እና መምሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱን አስመልክቶ የመምህራኑን ቀና (አዎንታዊ) አመለካከት የሚያሳዩ ሲሆኑ ከአማካዩ በታች የሆኑት ደግሞ አሉታዊ አመለካከት የሚያሳዩ ናቸው::

ሁለተኛው የምርምር ጥያቄ ለመመለስ አመቺ የሚሆነው መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምልከታ ነው:: በምልከታውም መረጃ ለመሰብሰብ ያመች ዘንድ ባለ ሶስት ነጥብ ስኬል ማመሳከሪያ ቅጽ ወይም እርከናዊ ልኬት (Rating Scale) ተዘጋጅቶ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል:: ይህም የምልከታ ቅጽ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ መምህራኑ በመርሃትምህርቱና በመምህር መምሪያው ውስጥ የሰፈሩትን የመማር ማስተማር መርህ ቅደም ተከተሎች (instructional guidelines) ተግባራዊ የማድረግ ወይም ያለማድረጋቸውን ሁኔታ በድግግሞሽ ቆጠራ (Frequency count) እና በመቶኛ ስሌት (percentage) ተንትኖ ለማሳየት አስችሏል::

ሶስተኛውንም የምርምር ጥያቄ ለመመለስ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን የድግግሞሽ ቆጠራ እና የመቶኛ ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል:: ከዚህም ሌላ አራተኛውን የምርምር ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ሲባል የተዘጋጀውን ፈተና 216

ተማሪዎች እንዲፈተኑ ከተደረገ በኋላ በሶስት አራሚዎች በጥንቃቄ ታርሞ ተማሪዎቹ ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ትንታኔ ተሰጥቷል:: ለትንታኔ አሰጣጡም መነሻ የሆነው "50% የማለፊያ ነጥብ ነው" የሚለው የአዲሱ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ ድንጋጌ ነው:: ከዚህም የማለፊያ ነጥብ አኳያ የወደቁና ያለፉ ተማሪዎችን ውጤት በመቶኛ በማስላት ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል:: እንዲሁም ከእያንዳንዱ የትምህርት ይዘት ወይም ክፍል አንጻር ካለፉና ከወደቁ ተማሪዎች ቁጥር አኳያ በትምህርትቤቶች (ወይም በዞኖች) መካከል ስታትስቲካዊ የሆነ ጉልህ ልዩነት (Significant diffrence) መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የ'chi-square ($x^2$) ስታትስቲካዊ ስሌት (test of independence) ከ 'alpha (α) 0.05 level of significance' ጋር በማቀናጀት ለመጠቀምና ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል::

ከዚህም ሌላ በጽሁፍ መጠይቆቹ ውስጥ የቀረቡት ደረጃ-ለክ (Rank-Order) ጥያቄዎችም ሆኑ ሌሎች ፍጻሜ-ክፍት (Open-ended) እና ፍጻሜ-ዝግ (Close-ended) ጥያቄዎች ለአምስተኛው የምርምር ጥያቄ ተገቢ ምላሽ መስጠት የሚያስችል መረጃ የሚያስገኙ ናቸው:: በጥያቄዎቹም አማካኝነት የተገኘውን መረጃ በመቶኛ ስሌትና ገላጭ (Descriptive) ዘዴ በመጠቀም ተገቢ የሆነ ትንተና ለመስጠት ጥረት ተደርጓል::

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

ይህ ምዕራፍ በተለያዩ ዘዴዎች - በጽሁፍ መጠይቅ፣ በክፍል ውስጥ ምልከታ እና በችሎታ መለኪያ ፈተና - አማካኝነት የተዘገበውን መረጃ በሰንጠረዥ አስደግፎ ለመተንተን እንዲሁም በአንዳንድ ማብራሪያዎች ለማስረዳት የሚሞከርበት ነው:: የትንተናውም አካሄድ የጥናቱን አበይት ጥያቄዎች ቅደም ተከተል የተከተለ ይሆናል::

### 4.1. <u>ስለመርሃትምህርቱ እና ስለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ መምህራኑ ያላቸው አመለካከት</u>

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ወስጥ እንደተጠቀሰው መምህራኑ ለመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ወይም ለስርዓተትምህርቱ የሚኖራቸው አመለካከት በትግበራው ውጤታማነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል:: ይህንንም ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የመምህራኑን አመለካከት ሊመዝኑ የሚችሉ ጥያቄዎች በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ ተካተዋል/አባሪ ለ. ክፍል ሁለትን ይመለከቷል/:: ከነዚህም ጥያቄዎች (statements) የተገኘውን መረጃ በሚከተለው ሰንጠረዥ አጫምቆ ለማቅረብ ተሞክሯል:

<u>ሰንጠረዥ 1</u>

<u>**የመምህራኑ አመለካከት ከጾታ ረገድ ሲታይ**</u>

| ምድብ | መጠይቁን የሞሉ መምህራን | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሴቶች | | ወንዶች | | ድምር | |
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ከአማካዩ በላይ | 5 | 38.5 | 2 | 28.6 | 7 | 35.0 |
| ከአማካዩ በታች | 8 | 61.5 | 5 | 71.4 | 13 | 65.0 |
| ድምር | 13 | 100.0 | 7 | 100.0 | 20 | 100.00 |
| $X^2 = 0.002$ | | | | | | |

በአጠቃላይ ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን ለመርሃትምህርቱ እና ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ነው:: ይህም በተግባራዊ ሂደቱ ላይ የራሱ የሆነ ተጽዕኖ ሊኖረው እንደሚችል አይካድም:: በሰንጠረዡም የሰፈረው መረጃ ለምርምሩ የመጀመሪያ ጥያቄ - ለክፍሉ ቋንቋውን የሚያስተምሩ መምህራን ለመርሃ ትምህርቱ እና ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ ምን አይነት አመለካከት ወይም ግንዛቤ አላቸው?- ተገቢ ምላሽ አስገኝቷል::

## 4.2. የመምህራኑ የማስተማር ሂደት

በመደበኛ ትምህርት ሂደት ( Formal education ) ውስጥ መማሪያ ክፍል አንዱና ዋንኛው የተስተምህሮ አውድ መሆኑ ይታወቃል:: ይህ አውድ መምህራን፣ ተማሪዎችና መርሃትምህርቱ እርስ በእርስ የሚገናኙበት ነው:: በመሆኑም የመምህራኑ የማስተማር ሁኔታ ወይም ሂደት የመርሃትምህርቱን ትግበራ አዎንታዊ ውጤት ወይም አሉታዊ ውጤት ሊወስን መቻሉ የሚካድ አይሆንም::

ይህንን ሁኔታ መሰረት በማድረግ በእርከናዊ ልኬት (Rating scale) አማካኝነት የስድስት መምህራንን የክፍል ውስጥ የማስተማር ሁኔታ ለመመልከትና መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሮ የሚከተለው ሁኔታ ተስተውሏል::

## ሰንጠረዥ 2

### በአርከናዊ ልኬት የተገኘ የክፍል ውስጥ የምልከታ ውጤት

| ተ.ቁ | የማስተማር ክንውን | በምልከታ የተገኘው ወጤት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በተደጋጋሚ | | አልፎ አልፎ | | አያደርግም | |
| | | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| 1 | የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ተማሪዎቹ እንዲያስታውሱ ያበረታታል/ታበረታታለች (ክለሳ ያደርጋል/ታደርጋለች) | 8 | 14.8 | 22 | 40.7 | 24 | 44.4 |
| 2 | የእለቱን ትምህርት ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተዋውቃል/ታስተዋውቃለች/ | 14 | 26.0 | 20 | 37.0 | 20 | 37.0 |
| 3 | የትምህርቱን አላማ ይገልጻል/ትገልጻለች | - | - | 3 | 5.5 | 51 | 94.4 |
| 4 | ተማሪዎች ተግባራትን/Tasks/ በቡድን እንዲሰሩ ያደርጋል/ታደርጋለች | - | - | - | - | 54 | 100.0 |
| 5 | የቡድን ስራውን እየተዘዋወረ ይቆጣጠራል /ትቆጣጠራለች | - | - | - | - | 54 | 100.0 |
| 6 | መርሃ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ ተግባራት በክፍል ውስጥ እንዲከናወኑ ለተማሪዎች ይሰጣል/ትሰጣለች | 3 | 5.5 | 21 | 38.9 | 30 | 55.6 |
| 7 | ተግባራት እንዴት መከናወን እንዳለባቸው ግልጽ የሆነ መግለጫ ለተማሪዎች ይሰጣል /ትሰጣለች | 19 | 35.2 | 34 | 63.0 | 1 | 1.9 |
| 8 | ለእያንዳንዱ ይዘት የሚያስፈልጉ የትመህርት መርጃ መሳሪያዎች ይጠቀማል/ትጠቀማለች | 1 | 1.9 | 1 | 1.9 | 52 | 96.3 |
| 9 | ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታታል (ባጫጭር ጥያቄና መልስ ያልተገደበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ተማሪዎችን ያበረታታል /ታበረታታለች) | 12 | 22.2 | 30 | 55.6 | 12 | 22.2 |
| 10 | ጠቃሚ ነጥቦችን በሰሌዳ ላይ ይጽፋል /ትጽፋለች | 20 | 37.0 | 17 | 31.5 | 17 | 31.5 |
| 11 | ምጋቤ ምላሽ (feed back) ከተማሪዎች ይጠይቃል/ትጠይቃለች | 40 | 74.1 | 13 | 24.1 | 1 | 1.9 |
| 12 | በቂ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች | 42 | 77.8 | 12 | 22.2 | - | - |
| 13 | የተማሪዎችን የቤት ስራም ሆነ የክፍል ስራ በማረም ይቆጣጠራል/ትቆጣጠራለች | 14 | 26.0 | 40 | 74.1 | - | - |
| 14 | የመማር ማስተማሩን ሂደት ተማሪ መራሽ (student center) ለማድረግ ይጥራል/ትጥራለች | - | - | 49 | 90.7 | 5 | 9.3 |
| 15 | የዕለቱን ትምህርት አስመልክቶ ማጠቃለያ ይሰጣል/ትሰጣለች | - | - | 1 | 1.9 | 53 | 98.1 |
| | ድምር | 173 | 21.4 | 263 | 32.5 | 374 | 46.2 |

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው በዝርዝር ከቀረቡት 15 የመማር ማስተማር ከንውን መርሆዎች (instructional guide lines) ውስጥ በተደጋጋሚ ተግባራዊ ሆነው የታዩት እጅግ በጣም ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው። እነሱም በተራ ቁጥር 10፣11 እና 12 ስር የተጠቀሱት ሆነው እናገኛቸዋለን። ማለትም የምልከታ ውጤቱ እንደሳየው መምህራኑ ጠቃሚ ነጥቦችን በሰሌዳ ላይ ይጽፋሉ። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 37 በመቶ ነው። መምህራኑ ከተማሪዎች ምጋቤ ምላሽ (feed back) የመጠየቃቸው ሁኔታ ደግሞ 74.1 በመቶ ድግግሞሽ አሳይቷል። ከዚህም ሌላ መምህራኑ ለተማሪዎች የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ 77.8 በመቶ ድግግሞሽ እንደታየበት ተረጋግጧል።

መምህራን እክፍል ገብተው የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸው በፊት አስቀድሞ ተማሪዎቹ የተማሩትን ነገር እንዲያስታውሱና እንዲከልሱ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህም ሁኔታ በመርሃትምህርቱና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ ሰፍሮ ወይም ተጠቅሶ እናገኛለን። ይሁን እንጂ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው መምህራኑ ሁኔታውን 40.7 በመቶ አልፎ አልፎ ተግባራዊ ያደርጋሉ፣ 44.4 በመቶ ደግሞ ፈጽሞ ተግባራዊ አያደርጉም። ይህም ሁኔታውን በተደጋጋሚ ተግባራዊ ከማድረግ ጋር (14.8 በመቶ) ሲነጻጸር እጅግ ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህም ሌላ የዕለቱን ትምህርት ግልጽ በሆነ መንገድ የማስተዋወቃቸው ሁኔታ ተደጋጋሚ ሆኖ የተገኘው 26 በመቶ ሲሆን 37 በመቶ ደግሞ አልፎ አልፎ በክፍል ውስጥ ተስተውሏል። ይሁን እንጂ 37 በመቶ በሆነ ደረጃ ሁኔታው( የዕለቱን ትምህርት ማስተዋወቅ) ፈጽሞ በክፍል ውስጥ አልታየም።

በመምህር መምሪያው ውስጥ ከሰፈሩት የማስተማር ቅደም ተከተሎች መካከል 'የትምህርቱን አላማ መግለፅ' የሚል ሀሳብ ሰፍሮ ይገኛል። ይሁን እንጂ የምልከታው ውጤት እንዳመለከተው ሁኔታው 94.4 በመቶ ተግባራዊ አልተደረገም። ከዚህም ሌላ ተማሪዎችን በቡድን በማድረግ ተግባራት (Tasks) እንዲያከናውኑ የማድረግና

የቡድኑንም የአተገባበር ሂደት የመቆጣጠር ሁኔታ ፈጽሞውንም( 100 በመቶ) በክፍል ውስጥ አልተስተዋለም:: ለዚህም ሁኔታ የሚቀርበው ምክንያት የተማሪዎች ቁጥር መብዛትና የመቀመጫዎቹ ለቡድን ስራ ያለመመቸት ነው:: ከዚህም ጋር ባልተናነሰ መልኩ የመርጃ መሳሪያዎች (Teaching aids) የመጠቀም ሂደት በክፍል ውስጥ 96.3 በመቶ በሆነ ደረጃ አልተስተዋለም:: በተጨማሪም የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ ተገቢውን ማጠቃለያ የመስጠት ሂደት 98.1 በመቶ በሆነ ደረጃ ተግባራዊ ያለመደረጉን የምልከታው ውጤት አመልክቷል::

በአጠቃላይ በመርሃትምህርቱና በመምህር መምሪያው ውስጥ የተጠቆሙት የመማር ማስተማር ክንውን መርሆዎች (instructional guidelines) በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ተገባራዊ ሆነው የተገኙት 21.4 በመቶ በሆነ መልኩ ብቻ ሲሆን 46.2 በመቶ ደግሞ ፈጽሞ ተግባራዊ ሆነው አልተገኙም:: ይህም ሁኔታ መርሃትምህርቱ በክፍል ውስጥ በብቃት ተግባራዊ መደረግ አለመቻሉን በግልጽ ያሳያል::

በክፍል ምልከታው እንደተስተዋለው የመምህራኑ የማስተማር ስልት ተመሳሳይነት ያለውና አንድ ወጥ የሆነ ነው:: ይሄውም ከመማሪያ መፅሀፉ ለተማሪዎች የቤት ስራ ይሰጣል፣ በማግስቱ በቤት ስራው መሰረት ጥያቄና መልስ ይካሄድና (መምህሩ ይጠይቃል፣ ተማሪዎች በተናጠል መልስ ይሰጣሉ) ተማሪዎቹ ያቃታቸውን መምህሩ ራሱ ይመልሳል፣ በመፅሀፉ መሰረት የምንባብ ክፍል ጋ ሲደረስ ተማሪዎች በየተራ ቆመው ጮክ ብለው ያነባሉ፣ ምንባቡን አስመልክቶ መምህሩ ማብራሪያ ይሰጣል:: ከዚያም በመፅሀፉ የቀረቡት መልመጃዎች በቤት ስራነት ይሰጣሉ:: ይህ አይነት የማስተማር ሂደት ነው በብዛት የተስተዋለው::

ስለዚህ የክፍል ውስጥ ምልከታው ውጤት እንደሚያሳየው የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ ተገቢ የሆነ አሉታዊ ምላሽ አግኝቷል ማለት ይቻላል::

በበቂ ሁኔታ ይገኛል። 20 በመቶ የሚሆኑት ግን በቂ አለመሆኑን ገልጸዋል። ለየት ባለ መልኩ የማስታወቂያ ሰሌዳን በተመለከተ ከመምህራኑ መካከል 65 በመቶዎቹ ፈጽሞ የለም፣ 25 በመቶዎቹ በቂ አይደለም፣ 10 በመቶዎቹ ደግሞ በቂ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

የሰሌዳ ማጥፊያ ዳስተርንም አስመልክቶ በርካታዎቹ መምህራን (60 በመቶ) በቂ መሆኑን ሲያረጋግጡ 30 በመቶ የሚሆኑት በቂ አለመሆኑን ይገልጻሉ። 10 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ፈጽሞ የለም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህም ሌላ ከብዙዎቹ መምህራን (75 በመቶ) ምላሽ ማረጋገጥ እንደሚቻለው በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ መርጃ መሣሪያዎች (Teaching aids) በበቂ ሁኔታ አያገኙም።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የትምህርት ቤቶቹ የመማሪያ ክፍል ውስጣዊ ገጽታ ምንም እንኳን የተጋነነ ባይሆንም ያልተሟላ ወይም በበቂ ቁሳቁስ ያልተቀናጀ መሆኑን ከአብዛኛዎቹ መምህራን ምላሽ መገንዘብ ይቻላል።

ሰንጠረዥ 4

<u>ለመማር ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ መሣሪያዎች አቅርቦት ሁኔታ</u>

| ለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ | የመምህራኑ (20 ) ምላሽ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በበቂ ሁኔታ | | ባልተሟላ ሁኔታ | | ፈጽሞ አይሰጥም | |
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| የትምህርት እቅድ (lesson plan) ማዘጋጃ ደብተር/ወረቀት | 16 | 80.0 | 4 | 20.0 | - | - |
| እስክርቢቶና ርሳስ | 4 | 20.0 | 13 | 65.0 | 3 | 15.0 |
| ለቴስት ማዘጋጃ የሚሆን ወረቀት | - | - | 14 | 70.0 | 6 | 30.0 |
| ለማስታወሻ መያዣ የሚሆን ወረቀት | 3 | 15.0 | 4 | 20.0 | 13 | 65.0 |
| ለተከታታይ ምዘናዎች ውጤት መመዝገቢያ የሚሆን ቅጽ(ፎርም) | 18 | 90.0 | 1 | 5.0 | 1 | 5.0 |
| ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎች | 4 | 20.0 | 15 | 75.0 | 1 | 5.0 |

ከዚህ ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል 80 በመቶዎቹ የትምህርት እቅድ ማዘጋጃ ደብተር/ወረቀት በበቂ ሁኔታ እንደሚቀርብላቸው ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከብዙዎች (65 በመቶ) ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው እስክርቢቶና ርሳስ በበቂ ሁኔታ አያገኙም፡፡ በመተመሳሳይ መልኩ ለቴስት ማዘጋጃ የሚሆን ወረቀት ባልተሟላ ሁኔታ እንደሚያገኙ 70 በመቶ የሚሆኑ መምህራን ገልጸዋል፡፡ 65 በመቶ የሚሆኑት መምህራን ደግሞ ለማስታወሻ መያዣ የሚሆን ወረቀት ፈጽሞ እንደማይሰጣቸው ጠቁመዋል፡፡ ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎችንም በተመለከተ በሰንጠረዥ 3 እንደታየው ሁሉ አቅርቦቱ ያልተሟላ መሆኑን ከ75 በመቶዎች መምህራን ምላሽ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለተከታታይ ምዘናዎች ውጤት መመዝገቢያ የሚሆን ቅጽ/ፎርም/ ግን በበቂ ሁኔታ እንደሚያገኙ ብዙዎቹ (90 በመቶ) ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው ለመማር ማስተማር ሂደት የሚያስፈልጉ ቁሳቀጠስ ትምህርት ቤቶቹ የሚያቀርቡት ባልተሟላ ሁኔታ መሆኑን የአብዛኛዎቹ መምህራን ምላሽ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ለርዕሳነ መምህራኑ ከቀረበውም የጽሁፍ መጠይቅ (አባሪ ሐ '25ኛ' ተራ ቁጥርን ይመለከቷል) ምላሽ ማረጋገጥ እንደተቻለው የመሳሪያዎቹ አቅርቦት ቢኖርም ባልተሟላ ሁኔታ ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ደግሞ በመምህራኑ ላይም ሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ውጤት ላይ መሰናክል ሊፈጥር እንደሚችል እሙን ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 5

**የመርሃትምህርትና የመምህር መምሪያ አቅርቦት ሁኔታ**

| አይነት | የመምህራኑ (20) ምላሽ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | እምን አለ | | የለም | |
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| መርሃትምህርት | 13 | 65.0 | 7 | 35.0 |
| የመምህር መምሪያ | 20 | 100.0 | | -- |

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው አብዛኞዎቹ (65 በመቶ) መምህራን መርሃትምህርት በትምህርትቤት እንደሚገኝ ሲገልጹ የመምህር መምሪያውን በተመለከተ ደግሞ ሁሉም መምህራን "አለ" የሚል መልስ ሰጥተዋል። ይሁን እንጂ በተማሪ መማሪያ መጽሀፉ የሰፈሩት ይዘቶች ሙሉ በሙሉ በመምህር መምሪያው ውስጥ በተሟላ አኳኋን አለመብራራታቸውን ብዙዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ገልጸዋል /ሰንጠረዥ 9'ን ይመለከቷል/።

ከዚህም ሌላ የመማሪያ መጻህፍትን አስመልክቶ ለተማሪዎች በምን ያህል ምጥጥን እንደሚደርሳቸው ለርዕሳነ መምህራኑ ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ መገንዘብ እንደተቻለው በተወሰኑት ትምህርት ቤቶች (33.3 በመቶ) ውስጥ አንድ መጽሀፍ ለሁለት ተማሪዎች ሲደርስ በአብዛኞዎቹ ትምህርት ቤቶች (66.7 በመቶ) ደግሞ አንድ መጽሀፍ ለአንድ ተማሪ ይደርሳል። ይሁን እንጂ በክፍል ምልከታ ወቅት ለመገንዘብ እንደተቻለው አብዛኞቹ ተማሪዎች መጽሀፍ የላቸውም፣ ወይም ከቤታቸው ይዘው አይመጡም። ለዚህም ሁኔታ መንስኤ የሆነው አብዛኛውን ጊዜ መምህራኑ የቤት ስራ እንጂ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት (Tasks) ወይም መልመጃዎች ለተማሪዎች አለመስጠታቸው ሊሆን ይችላል።

## ሰንጠረዥ 6

**የትምህርት ቤቶቹ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት፣ ለቋንቋው ትምህርት የሚያደርጉት የመርጃ መሣሪያዎች (Teaching aids) አቅርቦት /ዝግጅት መጠን**

| አማራጮች | የመምህራኑ (20) ምላሽ | |
|---|---|---|
| | ቁጥር | % |
| በበቂ ሁኔታ | 1 | 5.0 |
| በጥቂቱ | 18 | 90.0 |
| በፍጹም አላዘጋጀም | 1 | 5.0 |
| ትምህርት ቤቱ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል የለውም | - | - |
| ድምር | 20 | 100.0 |

በየትምህርት ቤቶች ውስጥ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት እንደሚገኙ ከሰንጠረዥ 6 ማወቅ ይቻላል:: ይሁን እንጂ ከአብዛኛዎቹ መምህራን (90 በመቶ) ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው ማዕከላቱ ለአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚያግዙ መርጃ መሣሪያዎች (Teaching aids) የሚያዘጋጁት በጥቂቱ ብቻ ነው::

ምንም እንኳን ማዕከላቱ በጥቂቱም ቢሆን የመርጃ መሣሪያዎች ቢያዘጋጁም በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት እንደተስተዋለው መምህራኑ ሲያስተምሩ ምንም አይነት መርጃ መሳሪያ አይጠቀሙም:: ይህ ሁኔታ ደግሞ መምህራኑ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ መርጃ መሣሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ወይም መርጃ መሣሪያ በመጠቀም ቋንቋን እንዴት ማስተማር እንደሚቻል ግንዛቤ የላቸውም ወደሚል ሃሳብ ሊያመራን ይችላል:: በመርሃትምህርቱ ላይ ደግሞ ለያንዳንዱ የትምህርት ይዘት የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች መጠቀም እንደሚገባ በእቅድ ደረጃ ተጠቁሞ ይገኛል::

## ሰንጠረዥ 7

**የመርሃትምህርቱን ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ በመምህራኑ መካከል የሚኖር የመረዳዳት ሁኔታ እና ከርዕሰ መምህር የሚደረግ ድጋፍ**

| ጥያቄዎች | አማራጮች | የመምህራኑ ምላሽ | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % |
| በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ባሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የስራ ልምድን የመለዋወጥና በስራ የመረዳዳት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ልማድ አለ? | አዎን አለ | 15 | 75.0 |
| | የለም | 5 | 25.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን አተገባበር በተመለከተ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ከእርስዎ ጋር በግል ወይንም በዲፓርትመንት እማካኝነት ምን ያህል ውይይት ያደርጋሉ? | ብዙ ጊዜ | 2 | 10.0 |
| | አልፎ አልፎ | 9 | 45.0 |
| | ፈ ጽ ሞ አያደርጉም | 9 | 45.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር በአመት ውስጥ ስንት ጊዜ እርስዎ በማስተማር ላይ እያሉ እክፍል በመግባት ይጎበኝዎታል? | አንድ ጊዜ | 1 | 5.0 |
| | ሁለት ጊዜ | 16 | 80.0 |
| | ሶስት ጊዜ | - | - |
| | አራት ጊዜ | - | - |
| | ፈ ጽ ሞ ገ ብ ተ ው አያውቁም | 3 | 15.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የአራተኛ ክፍልን የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ትግበራ የተሳካ (ውጤታማ) ለማድረግ በትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የተደረገልዎት ድጋፍ ምን ያህል ነው? | ከፍተኛ | 1 | 5.0 |
| | መካከለኛ | 9 | 45.0 |
| | ዝቅተኛ | 10 | 50.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |

ቀደም ሲል በክለሳ ድርሳን ውስጥ እንደተገለፀው የመርሃትምህርትን ትግበራ ስኬታማ ለማድረግ የተለያዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል። ሰንጠረዥ ሰባትም በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመርሃትምህርቱን ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ ምን ያህል እርስ በእርስ እንደሚረዳዱና ርዕሰ መምህራኑም ለትግበራው ምን ያህል እገዛ እያደረጉ እንደሚገኙ የሚያሳይ ነው።

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያላቸውን ልምድ የመለዋወጥና በስራ የመረዳዳት እንዲሁም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ልማድ እንዳለ አብዛኛዎቹ መምህራን (75 በመቶ) ገልጸዋል። ይሁን እንጂ 45 በመቶ ከሚሆኑት መምህራን ምላሽ መገንዘብ እንደሚቻለው የቋንቋውን ትምህርት አተገባበር በተመለከተ ርዕሳነ መምህራን ከመምህራኑ ጋር በግልም ሆነ በዲፓርትመንት የሚያደርጉት ውይይት አልፎ አልፎ ብቻ የሚከሰት ነው። እንደውም ፈጽሞ ውይይት እንደማያደርጉም መጠይቁን ከመለሱ መምህራን መካከል 45 በመቶዎቹ ገልጸዋል። ርዕሳነ መምህራኑም ለቀረበላቸው "ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተናጠል ወይም በዲፓርትመንት ስብሰባ አማካኝነት የቋንቋውን መማር ማስተማር ሂደት አስመልክቶ ውይይት አድርገው ያውቃሉ?" የሚል ጥያቄ ግማሾቹ (50 በመቶ ) "አዎን" የሚል ምላሽ ሲሰጡ ግማሾቹ (50 በመቶ) ደግሞ "አላውቅም" የሚል ማረጋገጫ ሰጥተዋል።

ከዚህም ሌላ 80 በመቶ የሚሆኑት መምህራን እንደገለፁት ርዕሳነ መምህራኑ የቋንቋውን መምህራን ቋንቋውን በማስተማር ላይ እያሉ የማስተማር ሂደታቸውን እክፍል በመግባት የሚገመግሙት በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ ምንም እንኳን ለርዕሳነ መምህራኑ "የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን በማስተማር ላይ እያሉ ክፍላቸው ገብተው ምልከታ አድርገው ያውቃሉ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም (100 በመቶ) "አዎን አውቃለሁ" የሚል ምላሽ የሰጡ ቢሆንም "ፈፅሞ ገብተው አያውቁም" በማለት የገለፁ መምህራንም (15 በመቶ) ይገኛሉ። ይህም ሁኔታ ርዕሳነ መምህራኑ ግምገማ የሚያካሂዱት የተወሰኑ መምህራንን ብቻ መሆኑን ይጠቁማል። ከዚህም ሌላ የመርሃ ትምህርቱን ትግበራ ውጤታማ ለማድረግ ርዕሳነ መምህራኑ የሚያደርጉት እገዛ ዝቅተኛ መሆኑን 50 በመቶ የሚሆኑት መምህራን፣ መካከለኛ መሆኑን ደግሞ 45 በመቶ የሚሆኑ መምህራን ሲገልፁ አንድ መምህር ብቻ "ከፍተኛ" በማለት ጠቁመዋል።

## ሰንጠረዥ 8

### በትምህርት ቤቶቹ ውስጥ የሚስተዋል የክፍለ ጊዜ ምደባ፣የተማሪዎች ብዛት እና መምህራኑ ያለባቸው የስራ ጫና

| ጥያቄዎች | አማራጮች | የመምህራኑ ምላሽ | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % |
| የአመቱን ትምህርት ለመሸፈን የተሰጠው የክፍለ ጊዜ መጠን | በቂ ነው | 16 | 80.0 |
| | በቂ አይደለም | 3 | 15.0 |
| | ከሚፈለገው በላይ ነው | 1 | 5.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| በየክፍሉ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አስከትሏል? | አዎን | 19 | 95.0 |
| | አላስከተለም | 1 | 5.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የሚያስተምሩበት የክፍለ ጊዜ ብዛት የስራ ጫና ፈጥሮብዎታል? | አዎን ፈጥሮብኛል | 16 | 80.0 |
| | አልፈጠረብኝም | 4 | 20.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |

ከሰንጠረዥ 8 መገንዘብ እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ መምህራን (80 በመቶ) የአመቱን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመሸፈን የተሰጠው የክፍለ ጊዜ መጠን በቂ እንደሆነ ገልጸዋል። በሳምንት ውስጥ የተመደበውም ክፍለ ጊዜ 5 መሆኑ

ተረጋግጧል። 95 በመቶ የሚሆኑት መምህራን የተማሪዎች ቁጥር መብዛት በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን ይገልጻሉ። በቁጥራቸውም ብዛት የተነሳ የተማሪዎችን ደብተር ለማረምና ለመቆጣጠር፥ የእያንዳንዱን ተማሪ ችግር ለማወቅና ለመርዳት፥ ተማሪዎችን በቡድን አስቀምጦ ተግባራትን ለማሰራት፥ የእያንዳንዱን ተማሪ ችሎታ በተገቢ መልኩ ለመገምገም እንዲሁም እያንዳንዱን ተማሪ ምንባብ ለማስነበብ እንደሚቸገሩ መምህራኑ በዝርዝር ገልጸዋል። ከዚህም ሌላ በተማሪዎች ብዛት የተነሳ በክፍል ውስጥ ከፍተኛ ሙቀት እንደሚፈጠርና ያም በተማሪዎች ላይ የእንቅልፍና የድካም ስሜት እንደሚፈጥር አስረድተዋል። ከርዕሳነ መምህራኑም ምላሽ በተገኘው መረጃ መሰረት በየትምህርት ቤቶቹ በአንድ ክፍል ውስጥ በአማካይ 85 ተማሪዎች ይገኛሉ።

ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ ከሠንጠረዡ እንደምንረዳው እንዲያስተምሩ የተመደቡበት የክፍለ ጊዜ ብዛት የስራ ጫና እንደፈጠረባቸው አብዛኛዎቹ መምህራን (80 በመቶ) ገልጸዋል። ከመምህራኑ ምላሽ ለመረዳት እንደተቻለውም ብዙዎቹ (85 በመቶ) በሳምንት ውስጥ 30 ክፍለ ጊዜ የያዙ ሲሆን 15 በመቶዎቹ ደግሞ በሳምንት 27 ክፍለ ጊዜ ይሸፍናሉ። ከዚህም ሌላ አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ከማስተማር ስራቸው በተጨማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ በሌሎች ስራዎች (በክበባት አስተባባሪነትና አባልነት፥ በክፍለ ትምህርት ተጠሪነት፥ በማዕከል ፕሮጀክት ስራ፥ በተለያዩ ኮሚቴዎች አባልነት፥ ወዘተ) ተመድበው እንደሚሰሩ ጠቁመዋል። ይህም የስራ ጫና በመምህራኑ ላይ መሰላቸትን በመፍጠር በመርሃትምህርቱ ትግበራ ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ጥላ እንደሚያጠላበት የማይካድ ነው።

## ሰንጠረዥ 9

**የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ እና የመምህራን ሁኔታ**

| ጥያቄዎች | አማራጮች | የመምህራን ምላሽ | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % |
| ለ4ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ | በጣም ውስብስብ ነው | 3 | 15.0 |
| | በመጠነኛ ሁኔታ ውስብስብ ነው | 4 | 20.0 |
| | መካከለኛ ነው | 13 | 65.0 |
| | በጣም ቀላል ነው | - | - |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| በተማሪ መማሪያ መጽሀፉ የሰፈሩት ይዘቶች በሙሉ በመምህር መምሪያው ላይ በተሟላ አኳኋን ተብራርተዋል? | አዎን | 7 | 35.0 |
| | በበቂ ሁኔታ አልተብራሩም | 13 | 65.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የተማሪውን መማሪያ መጽሀፍ እንደዋነኛ የማስተማሪያ መሳሪያ አድርገው ሁልጊዜ ይጠቀሙበታል? | አዎን | 17 | 85.0 |
| | ሁልጊዜ አልጠቀምም | 3 | 15.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| ከአዲሱ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር በተለያዩ አውደጥናቶች ወይም በሌላ መንገድ ትውውቅ አድርገዋል? | አዎን | 4 | 20.0 |
| | አላደረግሁም | 16 | 80.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| ከአዲሱ ስርዓተ ትምህርት አንጻር ስላሉት የስራ ድርሻ፣ ሀላፊነትና ግዴታ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ አለዎት? | አዎን አለኝ | 7 | 35.0 |
| | በመጠኑ አለኝ | 9 | 45.0 |
| | የለኝም | 4 | 20.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| አዲሱን መርሃትምህርት በብቃትና በተሳካ መንገድ ለመተግበር ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልገኛል ብለው ያስባሉ? | አዎን አስባለሁ | 19 | 95.0 |
| | የለም!አያስፈልገኝም | 1 | 5.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| አማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩት | በፍላጎት ነው | 7 | 35.0 |
| | ያለፍላጎት በመመደብ ነው | 13 | 65.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |

ይህ ሰንጠረዥ መምህራኑ የመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱን አስመልክቶ ምን አይነት አስተያየት እንዳላቸው፣ መጻህፍቱን በምን ያህል ደረጃ እንደሚጠቀሙበት፣ ከአዲሱ መርሃትምህርት ጋር ያላቸው ትውውቅና የትውውቅ ፍላጎት ምን እንደሚመስል እንዲሁም ቋንቋውን ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል የተገኘውን መረጃ አጣምቆ የሚያሳይ ነው።

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) መማሪያ መጽሀፉ ከክባድነትና ከቀላልነት አኳያ፣ መካከለኛ መሆኑን ሲገልፁ 15 በመቶዎቹ ግን በጣም ውስብስብ መሆኑን ይጠቁማሉ። ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች አራተኛ ክፍል የሚደርሱት ከታች በደንብ ሳያጣሩ ማለትም ማወቅ ያለባቸውን ሳያውቁ በመሆኑ በተገቢ ሁኔታ መልመጃዎችን ለመስራት እንደሚቸገሩ መምህራኑ ጠቁመዋል። የመምህር መምሪያውን በተመለከተ ደግሞ 65 በመቶዎቹ መፅሀፉ (መምሪያው) በተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሰፈሩትን ይዘቶች በተሟላ ሁኔታ እንደማያብራራ አስረድተዋል። ይሁን እንጂ 35 በመቶ የሚሆኑት ይዘቶቹ በተሟላ አኳኋን መብራራታቸውን ይገልጻሉ።

አብዛኛዎቹ መምህራን (85 በመቶ) እንደገለፁት መምህራኑ የተማሪውን መማሪያ መጽሀፍ እንደዋንኛ የማስተማሪያ መሳሪያ አድርገው ሁልጊዜ የሚጠቀሙበት ሲሆን 15 በመቶዎቹ ግን ሁልጊዜ አይጠቀሙበትም። ይሁን እንጂ በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት እንደተስተዋለው መምህራኑ ባጠቃላይ የቋንቋውን ትምህርት የሚያስተምሩት ሙሉ በሙሉ የተማሪ መማሪያ መፅሀፉን ብቻ በመጠቀም ነው። ከዚህም ሌላ ከጥቂቶቹ (20 በመቶ) በስተቀር 80 በመቶ የሚሆኑት መምህራን ከአዲሱ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርት ጋር በምንም አይነት መንገድ ትውውቅ አላደረጉም። በተጨማሪም አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ከአዲሱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አንጻር ምን አይነት የስራ ድርሻ፣ ሀላፊነትና ግዴታ እንዳላቸው ወይም ሊኖራቸው እንደሚገባ ሰፊና ግልፅ የሆነ ግንዛቤ የላቸውም። ይህ ደግሞ የስርዓተትምህርቱ ቀራጮች ወይም የመርሃትምህርቱ አዘጋጆች አዲሱን ስርዓተትምህርት የሚመለከት ስልጠና ለመምህራኑ የመስጠት ሃላፊነታቸውን መወጣት አለመቻላቸውን ያመለክታል።

ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ 95 በመቶ የሚሆኑ መምህራን መርሃትምህርቱን በብቃትና በተሳካ መንገድ ለመተግበር በአውደጥናት ወይም በክረምት መርሃግብር

ተጨማሪ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ 35 በመቶ ከሚሆኑት በስተቀር አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ቋንቋውን የሚያስተምሩት ያለፍላጎታቸው በመመደብ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በመርሃትምህርቱ ትግበራ ውጤታማነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል የሚካድ አይሆንም፡፡

## ሰንጠረዥ 10

### የትምህርት ቤቶቹ አደረጃጀትና የማስተማር ስርዓቱ (System) ተጽዕኖ

| ጥያቄዎች | አማራጮች | የመምህራኑ ምላሽ | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % |
| አሁን ያለው የትምህርት ቤትዎ አደረጃጀት በመርሃ ትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል ብለው ያምናሉ? | እዎን አምናለሁ | 7 | 35.0 |
| | በከፊል አምናለሁ | 7 | 35.0 |
| | አላምንም | 6 | 30.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| አሁን እየተጠቀሙበት ያለው ግለ መር (self-contained) የማስተማር ስልት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው ጠቀሜታ ምን ሆኖ አግኝተውታል? | አሉታዊ | 19 | 95.0 |
| | አዎንታዊ | 1 | 5.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው 35 በመቶ የሚሆኑት መምህራን የትምህርት ቤቱ አደረጃጀት በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረ ይገልጻሉ፡፡ ሌሎች 35 በመቶዎቹም ምንም እንኳን የተጽዕኖው መጠን ዝቅተኛ ቢሆንም አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ጠቁመዋል፡፡ ቀሪዎቹ መምህራን (30 በመቶ) ግን የትምህርት ቤቱ አደረጃጀት በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሌለው ገልጸዋል፡፡

በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ከ1ኛ-6ኛ ክፍል ድረስ ያለው የማስተማር ስርዓት(system) አህጻዊ ወይም ግለ-መር( self-contained) መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው አብዛኛዎቹ መምህራን (95 በመቶ) ይገልጻሉ፡፡ የአሉታዊነቱንም ለምንነት ሲገልፁ "አንድ መምህር በሁሉም የትምህርት አይነት ሙሉ በሙሉ ብቁ ሊሆን ስለማይችል ተማሪዎቹ ይጎዳሉ፣ በመምህሩ ላይም ሆነ በተማሪዎች ላይ መሰለቻቸትን ይፈጥራል፣ አንድ መምህር ለሁሉም የትምህርት ዓይነት እኩል ዝንባሌ (ፍላጎት) ስለማይኖረው የማይፈልገውን ትምህርት በጥራት ሊያስተምር ስለማይችል ተማሪዎች ይጎዳሉ፡፡" በማለት አስረድተዋል፡፡

እንግዲህ ከሰንጠረዥ 3 እስከ 10 ድረስ ያለው የመረጃ ትንተና ጥናቱ ሊመልሳቸው ካነሳቸው ጥያቄዎች መካከል ለሰስተኛው ጥያቄ ተገቢ ምላሽ የያዘ ነው፡፡ ይሄውም የትምህርት ቤቶቹ አጠቃላይ ሁኔታ መርሃትምህርቱን በተገቢ መልኩ ለመተግበር እምብዛም አመቺ አለመሆኑን ትንተናው ያሳያል፡፡

## 4.4. የተማሪዎቹ የፈተና ውጤት

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ፈተናው በመጀመሪያው መንፈቀ አመት ያሉትን የትምህርት ክፍሎች-ማንበብና ማስተዋል፣ ጽህፈት እና ስነልሳን-ብቻ ያካተተ ሲሆን የተፈተኑትም 216 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል አንጻርም ምን ያህል ተማሪ እንደወደቀና ምን ያህል እንዳለፈ በሚከተለው ሰንጠረዥ ማሳየት ይቻላል፡፡

## ሰንጠረዥ 11

## ከተለያዩ የትምህርት ክፍሎች አንጻር ከማለፊያ ነጥብ በላይና በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች

| የትምህርት ክፍል | የማለፊያ ነጥብና ከዛ በላይ ያገኙ | | ከማለፊያ ነጥብ በታች ያገኙ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ማንበብና ማስተዋል | 84 | 38.9 | 132 | 61.1 | 216 | 100.0 |
| ጽህፈት | 69 | 31.9 | 147 | 68.1 | 216 | 100.0 |
| ስነልሳን | 108 | 50.0 | 108 | 50.0 | 216 | 100.0 |

ከሰንጠረዥ መገንዘብ እንደሚቻለው ፈተናውን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ (61.5 በመቶ) የሆኑት በመጀመሪያው የትምህርት ክፍል (ማንበብና ማስተዋል) ወድቀዋል፡ ማለትም ከማለፊያ ነጥብ በታች አስመዝግበዋል፡፡ የማለፊያ ነጥብና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ 38.9 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ ጽህፈትንም በተመለከተ የማለፊያ ነጥብና ከዛ በላይ ያስመዘገቡት ጥቂት ተማሪዎች (31.9 በመቶ) ሲሆኑ አብዛኞዎቹ (68.1 በመቶ) ያገኙት ውጤት ከማለፊያ ነጥብ በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለየት ባለ መልኩ ደግሞ ስነልሳንን በተመለከተ 50 በመቶዎቹ የማለፊያ ነጥብና ከዚያ በላይ ሲያስመዘግቡ የቀሩት 50 በመቶዎቹ ወድቀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ከተጠቀሱት የትምህርት ክፍሎች አንጻር ሲታይ በስነልሳሥን ዘርፍ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ብዙ ተማሪዎች አልፈዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው በመርሃ ትምህርቱ ውስጥ ለስነልሳን ሰፋ ያለ ክፍለ ጊዜ ስለተመደበለትና መምህራኑም ለዚሁ ትኩረት ስለሚሰጡ ሊሆን ይችላል /ለእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የተመደበውን ክፍለ ጊዜ በተመለከተ አባሪ 'ሠ' ን ይመለከቷል/፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከት እያንዳንዱን የትምህርት ክፍል አስመልክቶ ከማለፊያ ነጥብ በታች ያስመዘገቡ ተማሪዎች በርካታ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ

የመርሃትምህርቱን በተገቢ ሁኔታ አለመተግበር ወይም ተግባራዊ አለመሆን የሚጠቁምና በዚህም ሳቢያ በመርሃትምህርቱ የተቀረጹትን አላማዎች ወይም የትምህርት ይዘቶች በታቀደው መልኩ ተማሪዎቹ መጨበጥ አለመቻላቸውን የሚያስረዳ ነው።

ከዚህም ጋር በተያያዘ መልኩ ተማሪዎቹ ካስመዘገቡት ውጤት አንጻር በተለያዩ ትምህርት ቤቶች መካከል ልዩነት ወይም ተመሳሳይነት መኖር አለመኖሩን በሚከተለው ሰንጠረዥ ማሳየት ይቻላል።

ከመረጃው የሚገኘው የ 'Chi-square ($X^2$) ስሌት ውጤት ከመደበኛው ውጤት (Chritical Chi-square value) ካነሰ ከተማሪዎቹ በፈተና የማለፍ እና የመውደቅ ደረጃ አኳያ በትምህርት ቤቶቹ መካከል ስታትስቲካዊ የሆነ ጉልህ ልዩነት (Significant difference) አለመኖሩን ያስረዳል።

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተውም ከሶስቱም የትምህርት ክፍሎች የተገኙት የ 'Chi-square' ስሌት ውጤቶች ( 3.974 ፥ 5.303 እና 2.664) ከመሰረታዊው የ 'Chi-square' ውጤት (df=5, P≤ 0.05, $X^2$=11.07) ያነሱ ናቸው። በመሆኑም በትምህርት ቤቶቹ (በዞኖቹ)መካከል ከተማሪዎች በፈተናው የመውደቅና የማለፍ ደረጃ አንጻር ስታትስቲካዊ የሆነ ጉልህ ልዩነት (Significant difference) የለም ብለን ማጠቃለል እንችላለን። ይህ ደግሞ በሁሉም ትምህርትቤቶች (ዞኖች) የመርሃትምህርቱ አተገባበር ተመሳሳይ መሆኑን የሚያሳይ ይሆናል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ደግሞ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት (ዞን) ፈተናውን ምን ያህል ተማሪዎች እንደወደቁና ምን ያህሉ እንዳለፉ በሚከተለው ሰንጠረዥ ማሳየት ይቻላል።

<u>ሰንጠረዥ 13</u>

<u>ከመደበኛው የማለፊያ ነጥብ (50%) አኳያ የወደቁና ያለፉ ተማሪዎች ብዛት</u>

| ትምህርት ቤቶች | ያለፉ | | የወደቁ | | ድምር | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁጥር | % | ቁጥር | % | ቁጥር | % |
| ደጃች ባልቻ አባነፍሶ | 13 | 36.1 | 23 | 63.9 | 36 | 100.0 |
| ሽመልስ ሀብቴ | 20 | 55.6 | 16 | 44.4 | 36 | 100.0 |
| መጋቢት 28 | 19 | 52.8 | 17 | 47.2 | 36 | 100.0 |
| ዳግማዊ ምኒሊክ | 18 | 50.0 | 18 | 50.0 | 36 | 100.0 |
| ኮልፌ የመጀመሪያ ደረጃ | 13 | 36.1 | 23 | 63.9 | 36 | 100.0 |
| ቃሊቲ የመጀመሪያ ደረጃ | 14 | 38.9 | 22 | 61.1 | 36 | 100.0 |
| ድምር | 97 | 44.9 | 119 | 55.1 | 216 | 100.0 |

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው ምንም እንኳን ፈተናውን ከወሰዱት ተማሪዎች መካከል 44.9 በመቶዎቹ አልፈው ከግማሽ በላይ የሆኑት (55.1 በመቶ) የወደቁ ቢሆንም በትምህርት ቤቶቹ (ዞኖቹ) መካከል የተወሰነ ልዩነት ይታያል። ለምሳሌ ከሽመልስ ሀብቴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዞን 2) እና ከመጋቢት 28 (ዞን 3) ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት (በቅደም ተከተል 55.6 በመቶ እና 52.8 በመቶ) ያለፉ ሲሆን ከዳግማዊ ምኒልክ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (ዞን 4) ተፈታኞች መካከል 50 በመቶዎቹ ሲያልፉ 50 በመቶዎቹ ደግሞ ወድቀዋል። በቀሩት ትምህርት ቤቶች (ዞኖች) ግን የወደቁት ከግማሽ በላይ ናቸው።

እንግዲህ ጠቅለል ባለመልኩ ስንመለከተው ከተፈተኑት ተማሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሆኑት ወድቀዋል። ይህም የመርሃትምህርቱ ትግበራ አመርቂ በሆነ መልኩ ውጤታማ አለመሆኑን የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ ከሰንጠረዥ 11 እስከ 13 የቀረቡት መረጃዎችና ትንታኔዎቻቸው ለዚህ ጥናት አራተኛ መሰረታዊ ጥያቄ-ከትግበራው በኋላ ተማሪዎቹ የሚጠበቀውን እውቀት ማዳበር ችለዋል?-ተገቢ ምላሽ ሰጥተዋል።

## 4.5. <u>በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ተላውጦዎች (factors)</u>

ለመምህራን በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ "ክፍል አምስት" መሰረት መምህራኑ በደረጃ ያስቀመጧቸውን ተላውጦዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ ምንነታቸውን መመልከት ይቻላል።

## ሰንጠረዥ 14

**በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደሩ ተላውጦዎች አማካይ (Mean) ውጤት እና የተጽዕኖ ደረጃ (Rank)**

| ተ.ቁ | በትግበራው ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች | የተጽዕኖው ደረጃ | |
|---|---|---|---|
| | | አማካይ (Mean) | ደረጃ (Rank) |
| 1 | ማስተማሪያ መሳሪያዎች (መርሃትምህርት፣የመምህር መምሪያ፣ወዘተ.) እጥረት | 8.90 | 12 |
| 2 | የተማሪ መጻህፍት እጥረት | 7.70 | 9 |
| 3 | ከትምህርት ቤቱ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚደረግ ድጋፍ ማነስ ወይም የመርጃ መሳሪያዎች አለመኖር | 8.85 | 11 |
| 4 | በመርሃትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእውቀት ደረጃ ጋር አለመመጣጠን (የትምህርቱ ከባድነት) | 5.40 | 5 |
| 5 | በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ብዛት | 4.00 | 2 |
| 6 | ከተለያዩ አስተዳደራዊ ክፍሎች ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን | 6.35 | 6 |
| 7 | አዲሱን መርሃትምህርት አስመልክቶ ለመምህራን የተሰጠ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመኖር | 4.55 | 3 |
| 8 | የክፍሉ ውስጣዊ ገጽታ (የሰሌዳው ጥራት፣የዴስኮች አቀማመጥ፣ወዘተ.) አመቺ አለመሆን | 7.40 | 8 |
| 9 | በመምህራን ላይ የሚኖር የስራ ጫና | 4.85 | 4 |
| 10 | የማስተማሪያ ስነዘዴው ግልጽ አለመሆን | 8.80 | 10 |
| 11 | መምህራን በአዲሱ መርሃትምህርት መሰረት እንግሊዘኛ ቋንቋ ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን | 7.30 | 7 |
| 12 | የተማሪዎቹ ቀደምት ችሎታ (Background knowledge) አናሳ መሆን | 3.75 | 1 |

ከሰንጠረዡ መገንዘብ እንደሚቻለው የተማሪዎቹ ቀደምት ችሎታ (Background knowledge) አናሳ መሆን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ አዲሱን መርሃትምህርት አስመልክቶ ለመምህራን የተሰጠ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመኖር፣ በመምህራን ላይ የሚኖር የስራ ጫና፣ በመርሃትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእውቀት ደረጃ ጋር አለመመጣጠን (የትምህርቱ ከባድነት) እና ከተለያዩ አስተዳደራዊ ክፍሎች ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ዝቀተኛ መሆን የሚሉት ተላውጠዎች ከአሉታዊ ተጽእኖ አድራሽነታቸው አኳያ በቅደም ተከተል ከ1-6 የተጠቀሱ ናቸው። እነኚሁ ተላውጠዎች፣ ለመምህራኑ በቀረበው ፍጻሜ-ክፍት (Open-ended) ጥያቄ ላይም /አባሪ ለ. 25ኛ ተራ ቁጥር እና ክፍል አራትን ይመለከቷል/ በዋናነት ተጠቁመዋል። ከነኚህም በተጨማሪ ተማሪዎች ምዘናን ባላማከለ ሁኔታ እስከ አራተኛ ክፍል መሸጋገራቸው (free promotion) እና የማስተማሩ ሂደት አህዳዊ ወይም ግለ-መር (Self-contained) መሆኑ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ላይ የሚፈጥረው የመሰላቸት መንፈስ በዋናነት የሚጠቀሱ ተላውጠዎች መሆናቸውን አብዛኞዎቹ መምህራን ጠቁመዋል።

ቀደም ሲል በሰንጠረዥ 8 እንደተመለከትነው 95 በመቶ የሚሆኑ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩን ሲገልጹ 80 በመቶ የሚሆኑ ደግሞ የሚያስተምሩበት የክፍለ ጊዜ ብዛት የስራ ጫና እንደፈጠረባቸው ጠቁመዋል። ከዚህም ሌላ በሰንጠረዥ 9 ውስጥ እንደምንመለከተው 80 በመቶ የሚሆኑ መምህራን ከአዲሱ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ጋር በምንም አይነት መንገድ ትውውቅ ካለማድረጋቸውም በተጨማሪ መርሃትምህርቱን በብቃትና በተሳካ መንገድ ለመተግበር ተጨማሪ ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው አብዛኞዎቹ መምህራን (95 በመቶ) ገልጸዋል። ይሄ ሁኔታ ደግሞ አሁን በሰንጠረዥ 14 ውስጥ የተገለፀውን መረጃ የሚያጠናክር ነው።

አሁንም ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው በተራ ቁጥር አንድ፣ ሶስት እና አስር የተገለጹት ተላውጠዎች (ሁኔታዎች) በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ ያላቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ዝቅተኛ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ከሰንጠረዥ 6 እንደተገነዘብነው የየትምህርት ቤቱ የትምህርት ማበልፀጊያ ማእከላት ለቋንቋው ትምህርት መርጃ መሳሪያ (Teaching aid) የሚያዘጋጁት ዝቅተኛ በሆነ ደረጃ ሆኖ ሳለ ለሁኔታው (ለተላውጠው) ዝቅተኛ የተጽዕኖ ደረጃ መስጠቱ የመምህራኑን የመርጃ መሳሪያ የመጠቀም ችሎታ አናሳነትና ለአገልግሎቱም ትኩረት ያለመስጠት ሁኔታን የሚያመለክት ይሆናል። ለርዕሰ መምህራን በተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ በ21ኛው ተራ ቁጥር ስር ለቀረበው ፍጻሜ-ክፍት (Open-ended) ጥያቄ ከተሰጡት ምላሾች መካከልም "መምህራኑ ቋንቋውን ለማስተማር መርጃ መሳሪያ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ግንዛቤ የላቸውም።" የሚል ምላሽ በአብዛኛው ተጠቅሶ ይገኛል። ይህም እላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ በይበልጥ ሊያጠናክር ይችላል። በሰንጠረዥ 2 ውስጥ እንደተመለከትነው ደግሞ መምህራኑ በክፍል ውስጥ 96.3 በመቶ በሆነ መልኩ የመርጃ መሳሪያ ፈጽሞ አለመጠቀማቸውን ልብ ይሏል።

ከዚህም በተጨማሪ በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደሩ ጉዳዮችን እንዲጠቁሙ ለርዕሳነ መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል። ከተገኘው ምላሽ ውስጥም "ከአዲሱ ስርዓተትምህርት አንጻር የመምህራን ስልጠና ዝቅተኛ መሆን፣ የትምህርት ቤቶች የውስጥ ቁሳቁስ በቂ አለመሆን፣ ከተማሪዎች እድሜና ችሎታ አንጻር የመርሃትምህርቱ ከባድነት እንዲሁም የተማሪዎች ምንም ሳያጣሩ በቀጥታ አራተኛ ክፍል መድረስ" የሚሉ ተላውጠዎች በተደጋጋሚ ተጠቅሰው ይገኛሉ።

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከት ለመምህራንም ሆነ ለርዕሳነ መምህራን በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ፍጻሜ-ክፍት(Open-ended ) ጥያቄዎች አማካኝነት የተገኙት ምላሾች በዚህ በደረጃ-ለክ(Rank-order) ጥያቄ የተገኘውን መረጃ

በተለያዩ አቅጣጫዎች እውነትነቱን ለመፈተሽ (Triangulate) አስችለዋል። ማለትም ምላሾቹ በደረጃ ለክ ጥያቄ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚጣመሩና በጣም የሚደጋገፉ ሆነው ተገኝተዋል። በመሆኑም በሰንጠረዥ 14 የቀረበው መረጃ ከሌሎችም ጋር በመመሳከር ለጥናቱ አምስተኛ ጥያቄ በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ሁኔታዎች (ተላውጦዎች) ምንድን ናቸው?-በቂ የሆነ ምላሽ አስገኝቷል።

# ምዕራፍ አምስት

## ጭምቅ(Summary)፥ ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች (Recommendations)

### 5.1. ጭምቅ ('Summary)

የዚህ ጥናት አላማ አማርኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች በማዕከላዊ ደረጃ የተዘጋጀው የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት በክልል 14 ውስጥ ከአተገባበር አንጻር ምን መልክ እንዳለው ማሳየት ነው። ጥናቱንም ለማካሄድ ገላጭ ቅኝት የጥናት ዘዴ (Descriptive survey approach) ተግባራዊ ከመደረጉም ባሻገር፥ በክልሉ የሚገኙት ስድስት ዞኖችና ከእያንዳንዳቸውም አንድ አንድ ትምህርት ቤት በድምሩ ስድስት ትምህርት ቤቶች በመረጃ ምንጭነት ተወስደዋል። ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከመምህራን፥ ከርዕሳነ መምህራንና ከተማሪዎች ለማግኘት ሲባልም የጽሁፍ መጠይቅ፥ የክፍል ውስጥ ምልከታ እና የብቃት መለኪያ ፈተና (Achievement test) በመሳሪያነት ተግባራዊ ተደርገዋል።

በመሳሪያዎቹም አማካኝነት የተገኘውን መረጃ በሚከተለው መልኩ ጨምቆ ባጭሩ ማቅረብ ይቻላል፤

1ኛ. መርሃትምህርቱን እና መማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱን አስመልክቶ አብዛኛዎቹ መምህራን (65 በመቶ) ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ሲሆን ቀና ወይም አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው 35 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው። ከዚህም ሌላ 65 በመቶዎቹ መምህራን ቋንቋውን የሚያስተምሩት በፍላጎት ሳይሆን ያለፍላጎት ተመድበው ነው።

2ኛ. በመርሃትምህርቱና በመምህር መምሪያው ላይ በእቅድ ደረጃ የሰፈሩት የመማር ማስተማር ክንውን መርሆዎች (Instructional guidelines) በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ተግባራዊ ሆነው የተስተዋሉት በዝቅተኛ ሁኔታ (21.4 በመቶ) ነው:: በምልከታውም ማስተዋል እንደተቻለው የመማር ማስተማሩ ሂደት በብዛት የሚከናወነው ለተማሪዎች ከመፅሀፍ ላይ የቤት ስራ በመስጠትና በቤት ስራው መልስ ላይ ጥያቄና መልስ በማካሄድ ነው (መምህሩ ይጠይቃል፣ ተማሪዎች መልስ ይሰጣሉ)::

3ኛ. ከአብዛኛዎቹ መምህራን ምላሽ መገንዘብ እንደተቻለው መርሃትምህርቱን በጥራትና በተገቢ ሁኔታ ለመተግበር እገዛ የሚያደርጉ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ቁሳቁስ በትምህት ቤቶች ውስጥ በበቂ ሁኔታ አልተሟሉም፣ ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎችም ለመምህራን የሚቀርቡት ባልተሟላ ሁኔታ ነው::

4ኛ. 65 በመቶ የሚሆኑት መምህራን፥ መርሃትምህርት በየትምህርት ቤቶቹ እንደሚገኝ ሲገልፁ ሁሉም መምህራን (100 በመቶ) የመምህር መምሪያው በእጃቸው እንደሚገኝ ጠቁመዋል:: ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ (65 በመቶ) እንደገለፁት በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች በሙሉ በመምህር መምሪያው ላይ በበቂ ሁኔታ አልተብራሩም::

5ኛ. 90 በመቶ የሚሆኑት መምህራን እንደገለፁት የትምህርት ቤቶች የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ለቋንቋው ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች (Teaching aids) በበቂ ሁኔታ አያዘጋጁም::

6ኛ. ምንም እንኳን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ባሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የስራ ልምድ የመለዋወጥና የመረዳዳት ልማድ እንዳለ ከአብዛኛዎቹ መምህራን (75 በመቶ) ምላሽ መረዳት ቢቻልም ርዕሳነ መምህራኑ የቋንቋውን ትምህርት

በተመለከተ ከመምህራኑ ጋር ብዙ ጊዜ ውይይት እንደማያደርጉ 90 በመቶ የሚሆኑት ጠቁመዋል፡ ለትግበራውም ውጤታማነት የርዕሳን መምህራኑ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑን 50 በመቶዎቹ ገልፀዋል::

7ኛ. አብዛኛዎቹ መምህራን (80 በመቶ) እንደገለፁት፡ የአመቱን ትምህርት ለመሸፈን የተሰጠው የክፍለጊዜ መጠን በቂ ነው:: ይሁን እንጂ የተማሪዎቹ ቁጥር ብዛት (በአንድ ክፍል ውስጥ በአማካይ 85 ተማሪ) በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ 95 በመቶዎቹ መምህራን ጠቁመዋል፡ መምህራኑም በሳምንት የያዙት የክፍለ ጊዜ ብዛት (ከ27-30) የስራ ጫና እንደፈጠረባቸው ከአብዛኛዎቹ (80 በመቶ) ምላሽ መረዳት ተችሏል::

8ኛ. አብዛኛዎቹ መምህራን እንደገለፁት ለክፍሉ የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በጣም የተወሳሰበ አይደለም፡ በጣምም ቀላል አይደለም:: ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በደንብ ሳያጣሩ (ማወቅ ያለባቸውን ሳያውቁ) አራተኛ ክፍል ስለሚደርሱ በመፅሀፉ ውስጥ ያሉትን መልመጃዎች ለመስራት በጣም ይቸገራሉ:: 80 በመቶ የሚሆኑት መምህራን እንደገለፁትም እንደዋንኛ የማስተማሪያ መፅሀፍ አድርገው ሁልጊዜ የሚጠቀሙት ይህንኑ መጽሀፍ ነው:: ይህም ሁኔታ በክፍል ምልከታ ወቅት ተረጋግጧል:: ማለትም አንድም መምህር ከተማሪው መማሪያ መፅሀፍ ውጪ ሌላ ማስተማሪያ ሲጠቀም አልታየም::

9ኛ. መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል ከአዲሱ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሃትምህርት ጋር በተለያየ መንገድ ትውውቅ ያደረጉት በጣም ጥቂቶቹ (20 በመቶ) ብቻ ናቸው:: አብዛኛዎቹም (95 በመቶ) እንደገለጹት መርሃትምህርቱን በብቃትና በተሳካ መንገድ ለመተግበር ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል::

10ኛ. የብቃት መለኪያ ፈተናውን (achievement test) ከተፈተኑት 216 ተማሪዎች መካከል የማለፊያ ነጥብና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡት ወይም ያለፉት 44.9 በመቶዎቹ ብቻ ሲሆኑ 55.1 በመቶዎቹ ወድቀዋል።

## 5.2. ማጠቃለያ (Conclusion)

ጥናቱ እንደጠቆመው የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ተገቢና ውጤታማ በሆነ መልኩ አልተተገበረም። ይህ ማለት ደግሞ በዕቅዱ (Intent) እና በተግባራዊው እውነታ መካከል ሰፊ ክፍተት አለ ማለት ነው። ይህም ክፍተት በተለያዩ ተላውጦዎች(variables) አሉታዊ ተጽእኖ የተነሳ የተከሰተ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል።

ከጥናቱ መገንዘብ እንደተቻለው የተማሪዎቹ ቀደምት ችሎታ (Background knowledge) አናሳ መሆን፣ በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ አዲሱን መርሃትምህርት አስመልክቶ ለመምህራኑ የተሰጠ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመኖር፣ በመምህራን ላይ የሚኖር የስራ ጫና፣ በመርሃትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእውቀት ደረጃ ጋር አለመመጣጠን (የትምህርቱ ከባድነት) እንዲሁም ከተለያዩ አስተዳደራዊ ክፍሎች ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ካሳደሩት ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚህም ሌላ በአዲሱ የትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት የሚከናወነው ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ ያለው ምዘናን ያላማከለ የክፍል ክፍል ዝውውር (direct or free promotion) እንዲሁም ግለ-መር ወይም አሀዳዊ (self-contained) የማስተማር ስልት በትግበራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረዋል።

አብዛኛዎቹ መምህራን ለመርሃትምህርቱና ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻህፍቱ ያላቸው ዝንባሌ ወይም አመለካከት አሉታዊ መሆንና የአብዛኛዎቹም መምህራን

ቋንቋውን እንዲያስተምሩ ያለፍላጎት መመደብ በትግበራው ሂደት ላይም ሆነ በውጤታማነቱ ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ጥላ መጣሉ የማይካድ ነው:: በመሆኑም ሁኔታው በትክክል አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ብሎ ከመናገርም አልፎ የአሉታዊነቱ ገጽታ በምን መልኩ እንደሆነ በግልጽ ለማሳየት በሁለቱ ጎራዎች ያሉ መምህራንን (ቀና አመለካከት ያላቸውና የሌላቸው እንዲሁም በፍላጎት የተመደቡና ያለፍላጎት የተመደቡ መምህራን) የአተገባበር ሂደት ለወደፊቱ በጥልቀት ማጥናት እንደሚያስፈልግ አጥኚው አምኖበታል::

ጠቅለል ባለ መልኩ ስንመለከተው ግን በመርሃትምህርቱ እቅድ (Intent) እና በተግባራዊው እውነታ መካከል ሰፊ ክፍተት አለ:: ይህ ሁኔታ ደግሞ አስፈላጊ የሆኑ የመፍትሄ ርምጃዎች እስካልተወሰዱ ድረስ እየቀጠለ መሄዱ አይቀሬ ነው:: የዚህ ጥናት አቅራቢም ከጥናቱ ግኝት በመነሳት መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ የሚላቸውን ጥቂት ሀሳቦች እንደሚከተለው ይጠቁማል::

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳቦች (Recommendations)

1. በትግበራው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ካሳደሩት ሁኔታዎች መካከል አንዱና ዋንኛው የተማሪዎቹ ቀደምት ችሎታ (Background knowledge) ዝቅተኛ መሆን ነው:: ይህንን ሁኔታ ለማስወገድ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል የሚከናወነው ምዘናን ያላማከለ የክፍል ክፍል ዝውውር (free or direct promotion) ቀርቶ ተማሪዎቹ በየደረጃው ያሉትን የትምህርት ይዘቶች እያጣሩ እንዲመጡ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል::

2. የዞን ትምህርት መምሪያዎች፣ ተገቢ ከሆኑ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር የመርሃ ትምህርቱን አተገባበር አስመልክቶ በየጊዜው በአውደ ጥናት መልክ መምህራኑን ቢያሰለጥኑ በመርሃ ትመህርቱ እቅድና በመምህራኑ የአተገባበር ሂደት መካከል ያለው ክፍተት ሊወገድ ይችላል::

3. በምልከታ እንደተስተዋለው ሁሉም መምህራን ተማሪዎችን በቡድን በማስቀመጥ ተግባራት በክፍል ውስጥ ሲያሰሩ አልታየም። ለዚህም የሚቀርቡት ምክንያቶች "የተማሪዎቹ ቁጥር ብዙ መሆን እና የመማሪያው መፅሀፍ የቡድን ስራን የሚጋብዝ አለመሆን" የሚሉ ናቸው። ይሁን እንጂ አገራችን አሁን ካለችበት የኢኮኖሚ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን ብዛት ለመቀነስ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መምህራኑ ተማሪዎቹን በቡድን ስራ (group work) እንዴት ማስተማር እንደሚችሉ አጭር ስልጠና ቢሰጣቸው እንዲሁም አህጻዊው ዘዴ ወደ አበር-አስተምህሮ (Team teaching) ቢቀየር ችግሩ ሊፈታ ይችላል። ከዚህም ሌላ መፅሀፉ ተማሪዎቹን በሚመጥን መልኩ ለቡድን ስራ አመቺ የሆኑ ተግባራትን በማካተት እንደገና ተሻሽሎ መቅረብ ይኖርበታል።

4. በጥናቱ እንደተረጋገጠው የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት—ምንም እንኳን በቂ ባይሆንም—መርጃ መሣሪያዎች (Teaching aids) በመጠኑ ያዘጋጃሉ። ይሁን እንጂ መምህራኑ መርጃ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ ሲጠቀሙ አልታየም። በመሆኑም መምህራኑ ቋንቋን ለማስተማር መርጃ መሣሪያዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ተገቢ የሆነ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል።

## ዋቢ ጽሁፎች (References)

### ሀ. እንግሊዝኛ ምንጮች

#### ሀ. 1. መጻህፍት


Anderson, L. W. 1991. Increasing Teacher Effectiveness. Paris: Imprimerie Gauthieer-villais.

Baker, E.L. 1974. "Formative Evaluation of Instruction", in Popham, W.J. (ed.). Evaluation in Education. Barkeley: McCutehan Publishing Corporation.

Bohla, H.S. 1979. Evaluating Functional Literacy. Tehran: Hulton Educational Publications, Ltd.

Brown, H.D. 1994. Principles of Language Learning and Teaching. 3rd ed. Englewood Cliffs, NewJersey: Prentice Hall Regents.

Burrough, G. 1975. Design and Analysis in Educational Research. 2nd ed. Oxford: Alden Press.

Clark, C.M. and P.L. Peterson. 1986. "Teachers Through Processes", in Wittrock, M.C. (ed. ). Handbook of Research on Teaching. 3rd ed. New York: MaCMillan Publishing Company.

Doll, R.C. 1977. Curriculum Improvement: Decision Making and Process. 3rd ed. Boston: Allyn and Bacom, Inc.

Fullan, M. 1991. The New Meaning of Educational Change. London: Cassell Educational, Ltd.

__________. 1992. The New Meaning of Educational Change. London: Cassel Educational, Ltd.

Gironx, H.A. and et al. (eds.). 1981. Curriculum and Instruction. Berkeley: McCuthan Publishing Corporation.

Gross, N. and et al. 1971. Implementing Organizational Innovations: A Sociological Analysis of Planned Educational Change. New York: Harper and Row Publishers.

Grotelueschen, A.D. 1982. "Program Evaluation", in Knox, A. B. and et al (eds.) Developing, Administering and Evaluating Adult Education. SanFrancisco: Jossey Bass Publishers.

Hall, G. 1995. "The Local Educational Change Process and Policy Implementation", in Carter, D. and H.O. Marine.(eds.). International Perspectives on Educational Reform and Policy Implementation. London: The Falmer Press.

Hawes, H. 1979. Curriculum and Reality in African Primary Schools. London: Longman Group, Ltd.

Hiemstra, R. 1976. "Program Planning and Evaluation", in Goodman, S.E.(ed.). Handbook of Contemporary Education. New York: R.R. Bowker Co.

Hord, S. 1995. "From Policy Classroom Practice: Beyond the Mandates", in Carter, D. and H.O. Marine.(eds). International Perspectives on Educational Reform and Policy Implementation. London: The Falmer Press.

Jacobson, D. 1989. Methods for Teaching: A Skills Approach. 3rd ed. New Jersey: MaCmillan Publishing Company.

Klein, M.F. 1981. "Instructional Decisions in Curriculum", in Giroux, H.A. and et al. (eds). Curriculum and Instruction. Berkeley: McCutchan Publishing Corporation.

Lewy, A. (ed). 1977. Handbook of Curriculum Evaluation. Paris: Unesco Press.

Lewy, A. 1977. Planning the School Curriculum. Paris: UNESCO Press.

Madsen, H.S. 1983. Techniques in Testing. Oxford : OUP.

Marsh, C.J. 1992. Key Concepts for Understanding Curriculum. London: The Falmer Press.

McCormick, R. and M.James. 1989. Curriculum Evaluation in Schools, 2nd ed. London: Croom Helm, Ltd.

McNeil, J.D. 1990. Curriculum: A Comprehensive Introduction. 4th ed. U.S.A. Harper Collins Publisher.

Morris, L.L. and C.T. Fitz-Gibbon. 1978. Evaluators Hand Book. London: Sage Publications, Ltd.

Morris, L.L. and C.T. Fitz-Gibbon. 1978. How to Measure Program Implementation. London: Sage Publications Ltd.

Nunan, D. 1988. Syllabus Design. Oxford: OUP.

Oliva, P.F. 1988. Developing the Curriculum. 2nd ed. London: Scott, Foresman and Company.

Ornstein, A.C. and F.P. Hunkins. 1988. Curriculum: Foundations, Principles and Issues. Englewood Cliffs, New Jersey: Prentice Hall Inc.

__________. 1998. Curriculum: Foundation, Principles and Issues. 3rd ed. Boston: Alley and Bacon.

Patton, M.Q. 1979. "Evaluation of Program Implementation", in Sechrest, L. and et al. (eds.) Evaluation Studies: Review Annual, Vol.4. London: Sage Publications Ltd.

Posner, G.J. 1992. Analyzing the Curriculum. New York: McGraw Hill, Inc.

Pratt, D. 1980. Curriculum: Design and Development. San Diego: Harcourt Brace Jovanovich Publishers.

Provus, M. 1971. Discrepancy Evaluation for Educational Program Implement and Assessment. Berkeley: McCutchan Publishing Corporation.

Richards, J.C. and D.Nunan. 1990. Second Language Teacher Education. Cambridge: CUP.

Ross, K.N. and T.N. Postlethwaite. 1992. Indicators of the Quality of Education: A Summary of A National Study of Primary Schools in Zimbabwe. Paris: International Institute for Educational Planning Printshop.

Sampath, K. and et al. 1984. Introduction to Educational Technology. New Delhi: Sterling Publishers Pvt. Ltd.

Saylor, J. and et al. 1981. Curriculum Planning for Better Teaching and Learning. 4th ed. New York: Holt Rinehart and Winston.

Shiundu, J.S. and S.J.Omulands. 1992. CURRICULUM: Theory and Practice in Kenya. Nairobi: Oxford University Press.

Snyder, J. and et al. 1996. "Curriculum Implementation", in Jackson, P.W.(ed.). Handbook of Research on Curriculum. New York: MaCMillan.

Stenhouse, L. 1975. An Introduction to Curriculum Research and Development. London: Heinemann Educational Books Ltd.

Stern, H.H. 1992. Issues and Options in Language Teaching. Oxford: OUP.

Stufflebeam, D. 1983. "CIPP Model for Program Evaluation", in Goerge, M. and M.Scriven. (eds.). Evaluation Models. Boston: Kluwer-Nijhoff.

Tamir, P. 1981. "The Potential of Evaluation in Curriculum Implementation", in Lewy, A. and N. David (eds.). Evaluation Roles in Education. London: Gordon and Breach.

UNESCO. 1978. Planning the Primary School Curriculum in Developing Countries. Paris: International Institute for Educational Planning.

Ur, P. 1998. A Course in Language Teaching : Practice and Theory. Cambridge: CUP.

Wallace, M.J. 1991. Training Foreign Language Teachers. Cambridge: CUP.

Williams, W. 1978. "Implementation Analysis and Assessment", in Cook, T.D. and et al. (eds). Evaluation Studies: Review Annual, Vol. 3, London: Sage Publication.

Worthen, B.R. and J.R. Saunders. 1987. Educational Evaluation: Alternative Approaches and Practical Guidelines. New York: Longman, Inc.

Yalden J.C 1978 Principles of Course Design for Language Teaching. Cambridge. CUP.

Yeoman, G.O. and A.W. Back. 1987. Curriculum Evaluation, Study Guide 10. Nottingham: Nottingham University School of Education Publications Department.

Yoloye, E.A. (ed. ) 1978. Evaluation for Innovation: African Primary Science Programme Evaluation Report. Ibadan: Ibadan University Press.

## ሀ. 2. መጣጥፎች (Journals)

Aldrich, R.A. 1974. "Innovative Evaluation of Education", Theory into Practice. Vol. 13, No. 1.

Barger, R. 1974. "Evaluation and Decision Making for the Classroom", Theory in to Practice. Vol. 13, No. 1

Berman, P. and M.W. Mclaughlin. 1976. "Implementation of Educational Innovation", Educational Form, Vol. 11.

Caillods, F. and T.N. Postlethwaite. 1989. "Teaching-Learning Conditions in Developing Countries", Prospects: Quarterly Review of Education Vol. 29, No. 2

Dervegt, R.V. and H.Knip. 1990. "Beyond Implementation Series: Implementing Mandated Change. The School as Change Contractor", Curriculum Inquiry. Vol 20, No. 2.

Evans, R. 1993. "The Human Face of Reform." Educational Leadership. Vol. 51, No. 1.

Fullan, M. and A. Pomfret. 1977. Research on Curriculum and Instruction Implementation.", Review of Educational Research. Vol. 47, No. 2.

Hall, G.E. and S.F. Loucks, 1975. "Levels of Use of the Innovation: A Frame Work for Analysing Innovation Adoption." Journal of Teacher Education, Vol. 26, No. 1.

Lange, R.E. 1974. "A Search for Utility in New Evaluation Thought", Theory into Practice. Vol.13, No.1.

Langenbach, M. 1972. "Development of an Instrument to Measure Teachers' Attitudes towards Curriculum use and Planning", Journal of Educational Research, Vol. 66, No. 1.

Macdonald, B. 1971. "The Evaluation of the Humanities Curriculum Project: A Holistic Approach", Theory into Practice, Vol. 10, No.3

Parsons, C. 1976, "The New Evaluation: A Cautionary Note", Journal of Curriculum Studies, Vol. 8, No.2.

Saunders, M. and G. Vulliamy. 1983. "The Implementation of Curriculum Reform: Tanzania and Papua New Guinea", Comparative Education Review. Vol. 27, No. 3.

Stake, R.E. 1967. "The Countenance of Educational Evaluation", Teachers College Record, Vol. 68. No. 7.

Stufflebeam, D.L. 1973. "The Context, Input, Process, and Product Model of Evaluation", The Educational Technology Review Series, Vol. 11.

Tyler, R.W. 1974. "Utilizing Research in Curriculum Development", Theory into Practice. Vol. 13, No. 1.

## ሀ. 3. ያልታተሙ ሰነዶች

Dawit Mekonnen. 1999. ":An Evaluation on the Implementation of Seventh Grade English Syllabus in Eastern Gojjam" Master's thesis: Addis Ababa University.

Hailu Dinka. 1991. "Assessment of teachers Performance in Curriculum Implementation (Illubabor Senior Secondary School in Focus)". Master's Thesis: Addis Ababa University.

ICDR. 1998. Formative Evaluation of the Tryout Project of the New Curriculum Materials; Content Analysis. Addis Ababa:. CEERC.

Mekasha Belete. 1991. "Evaluation of the Implementation of Health Education through New Yenuro Zedey Syllabus." Addis Ababa University.

Melese Bedane. 1992. "An Evaluation of Grade 9-12 English Curriculum and its Implementation in Schools at Capitals of Ethiopians Administrative Regions as Cause for Students Deficience in English.", Master's Thesis: Addis Ababa University.

Solomon Ariaya. 2000. "The Evaluation of Implementation of Grade Eight Mathematics Syllabus in SNNP Region: with Specific Reference to Sidama Zone". Master's thesis: Addis Ababa University.

## ለ. አማርኛ ምንጮች


ሥርዓተ-ትምህርት:: 1989:: የአማርኛ ቋንቋ መርሐ-ትምህርት: 4ኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፡ ሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.ተ

ታደሰ ሲባሞ:: 1992:: በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የአማርኛ ቋንቋ ለሚማሩ የ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (1ኛ-4ኛ) ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ መርሃትምህርት ትግበራ ግምገማ (በሲዳማ ዞን በ4ኛ ክፍል ናሙናነት):: አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (የማስተርስ ቴሲስ) ያልታተመ::

ትምህርት ሚኒስቴር:: 1986:: የትምህርት ስልጠና ፖሊሲ ረቂቅ:: አዲስ አበባ፡ ት.መ.ማ.ማ.ድ.

__________:: 1986:: አጠቃላይ የሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ግምገማ ፕሮጀክት ሪፖርት:: አዲስ አበባ(ያልታተመ)::

አዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ት/ቢሮ:: 1991:: አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 4ኛ ክፍል:: አዲስ አበባ ፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

__________-:: 1991:: የመምህር መምሪያ 4ኛ ክፍል:: አዲስ አበባ፡ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት::

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

## ለመምህራኑ ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ ክፍል አንድ የተገኘ መረጃ

| የጥያቄ አይነቶች | አማራጮች | የመምህራኑ ምላሽ | |
|---|---|---|---|
| | | ቁጥር | % |
| ጾታ | ሴት | 13 | 65.0 |
| | ወንድ | 7 | 35.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| እድሜ | ከ20-24 | 3 | 15.0 |
| | ከ25-29 | 1 | 5.0 |
| | ከ30-34 | 3 | 15.0 |
| | ከ35-39 | 5 | 25.0 |
| | ከ40-44 | 1 | 5.0 |
| | ከ45-49 | 5 | 25.0 |
| | ከ50 በላይ | 2 | 10.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| የትምህርት ደረጃ | 12+TTI | 13 | 65.0 |
| | 12+1 | 5 | 25.0 |
| | 12ኛ ክፍል ብቻ | 1 | 5.0 |
| | 10+2 | 1 | 5.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| በመምህርነት ያገለገሉበት ዘመን (ዓመት) | ከ10 በታች | 3 | 15.0 |
| | ከ10-14 | 3 | 15.0 |
| | ከ15-19 | 5 | 25.0 |
| | ከ20-24 | 2 | 10.0 |
| | ከ25-29 | 3 | 15.0 |
| | ከ30-34 | 4 | 20.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| በአሁኑ ወቅት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ የሚያስተምሩት የትምህርት ዓይነት አለ? | አዎን | 20 | 100.0 |
| | የለም | - | - |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| በአንድ ሳምንት ያለዎት የክፍለ ጊዜ ብዛት | 30 | 17 | 85.0 |
| | 27 | 3 | 15.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |
| ከማስተማር ስራዎ በተጨማሪ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሌሎች ስራዎች ተመድበው ይሰራሉ? | እሰራለሁ | 13 | 65.0 |
| | አልሰራም | 7 | 35.0 |
| | ድምር | 20 | 100.0 |

አባሪ ለ

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ
## መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና
## ስነጽሁፍ ክፍል /TEAM/

በክልል 14 በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ላይ ባሉ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

የተከበሩ መምህር:

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ያለው የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት /syllabus/ ከአፈጻጸም ወይም ከአተገባበር አኳያ ምን መልክ እንዳለው መረጃ መሰብሰብ ብቻ ነው። ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ ለዚሁ ጥናት ብቻ የሚውል ይሆናል። ስለዚህ ለጥናቱ ውጤታማነት የእርስዎን በግልጽነት የተሞላ እውነተኛ ምላሽ አጥኚው በትህትና ይጠይቃል። ስለመልካም ትብብርዎም በቅድሚያ ምስጋና ይድረስዎ።

ማስታወሻ:

1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም።
2. መጠይቁን ከሌላ ሰው ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ በግል መሞላት ይኖርበታል።

ክፍል አንድ: ከዚህ በታች ያሉትን ባዶ ቦታዎች ጥያቄዎቹን መሰረት በማድረግ በተገቢ ምላሽ ያሟላቸው፡ አማራጮች ላሏቸው ጥያቄዎች ደግሞ የእርማት ምልክት /✓/ በማድረግ ምርጫዎን ያመልክቱ

የትምህርት ቤቱ ስም ______________________

ዞን ________ ወረዳ ________ ቀበሌ _____

1. ጾታ:- ወንድ______ ሴት _____
2. ዕድሜ______
3. የትምህርት ደረጃ____________

4. በመምህርነት ያገለገሉበት ዘመን ______________

5. በአሁኑ ወቅት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ የሚያስተምሩት የትምህርት አይነት አለ?

   አዎን ________ የለም ________

   ካለ ስሙን ይጠቀሱ ________________________________

6. በአንድ ሳምንት ያለዎት የክፍለ ጊዜ ብዛት ____________

7. ከማስተማር ስራዎ በተጨማሪ በትምህርት ቤቱ ውስጥ በሌሎች ስራዎች ተመድበው ይሰራሉ?

   እሰራለሁ __________ አልሰራም __________

8. በተራ ቁጥር "7" ሥር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "እሰራለሁ" የሚል ከሆነ፣ የስራውን ዓይነት ይጥቀሱ፤

________________________________________________

________________________________________________

ክፍል ሁለት፡ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ለሚገኙት አረፍተ ነገሮች ከተሰጡት አምስት አማራጭ ቁጥሮች መካከል "የእኔ አመለካከት ነው" ብለው የሚያስቡትን አንድ አማራጭ ብቻ በመምረጥ በአማራጭ ቁጥሩ አንጻር ይህን የእርማት ምልክት /✓/ በማድረግ ያሳዩ።

የአማራጭ ቁጥሮቹም ትርጓሜ የሚከተለው ይሆናል፡፡

5. በጣም እስማማለሁ
4. እስማማለሁ
3. መወሰን ያዳግተኛል
2. አልስማማም
1. በፍጹም አልስማማም

| ተ.ቁ | አረፍተ ነገሮች | አማራጭ ቁጥሮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | አሁን እየተሰራበት ያለው የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት /4ኛ ክፍል/ ከማስተማር ዝግጅት አኳያ በመምህራን ላይ የስራ ጫና ያሳድራል፡፡ | | | | | |
| 2 | በመርሀትምህርቱና በመምህር መምሪያው ላይ የተገለጹት ዓላማዎች ብዙዎቹ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህር መምሪያ መምህራኑ የማስተማር ስልታቸውን በቅድሚያ ለማቀድ እንዲችሉ እገዛ አያደርግም፡፡ | | | | | |
| 4 | ከይዘት አደረጃጀት አኳያ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መርሀትምህርት ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ ነው፡፡ | | | | | |
| 5 | በ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በአብዛኛው ለተማሪዎች ይከብዳሉ፡፡ | | | | | |
| 6 | ለ4ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት ከአቀራረጹ አንጻር መምህራን በልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ቴክኒኮች ተጠቅመው የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲያዳብሩ ያስችላል፡፡ | | | | | |
| 7 | አሁን ያለው የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት የመምህራንን ሀሳብና አስተያየት ያካተተ በመሆኑ ትግበራውም ውጤታማ ይሆናል፡፡ | | | | | |
| 8 | የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በዚሁ ክፍል ካሉ ሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ጎናዊ ግንኙነት ወይም ተያያዥነት በጣም የጎላ ነው፡፡ | | | | | |
| 9 | ለ4ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ያለመምህሩ እገዛ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡ | | | | | |
| 10 | ለ4ኛ ክፍል የቀረቡት የቋንቋ ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ ደረጃቸውን ጠብቀው የተዋቀሩ አይደሉም፡፡ | | | | | |
| 11 | በመርሀትምህርቱ ውስጥ የተነደፉት አላማዎች በተሟላ ሁኔታ ሊተገበሩ አይችሉም፡፡ | | | | | |
| 12 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ወይም ተግባሮች /Tasks/ ተማሪዎችን የሚመጥኑና በተማሪዎችም መካከል የውይይት መንፈስ የሚፈጥሩ አይደሉም፡፡ | | | | | |

ክፍል ሦስት

3.1. ከዚህ በታች የቀረቡት ጥያቄዎች ግማሾቹ በምርጫ የሚመለሱ፣ ግማሾቹ ደግሞ የእርስዎን የተሟላ ሀሳብ በመጻፍ የሚመለሱ ናቸው። በመሆኑም የምርጫ ጥያቄዎቹን የአማራጮቹን ፊደል በመክበብ፣ ባዶ ቦታ ያላቸውን ደግሞ በራስዎ ሀሳብ በመሙላት ስምምነትዎን ያሳዩ።

1. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት በእጅዎ ወይም በትምህርት ቤቱ አለ?

ሀ. አለ ለ. የለም

2. ለዚሁ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህር መምሪያ በእጅዎ ወይም በትምህርት ቤቱ ይገኛል?

ሀ. አዎን ይገኛል ለ. የለም አይገኝም

3. በተራ ቁጥር "2" ሥር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "የለም" የሚል ከሆነ የማስተማሩን ስራ እንዴት እያቀዱት ነው? በምንስ እየተመሩ ነው?

________________________________________

________________________________________

4. የአመቱን ትምህርት ለመሸፈን የተሰጠው የክፍለ ጊዜ መጠን

ሀ. በቂ ነው ለ. በቂ አይደለም ሐ. ከሚፈለገው በላይ ነው

5. አዲሱን መርሀትምህርት በብቃትና በተሳካ መንገድ ለመተግበር ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልገኛል ብለው ያስባሉ?

ሀ. አዎን አስባለሁ ለ. የለም! አያስፈልገኝም

"ያስፈልገኛል" ካሉ በምን አይነት መንገድ ____________________

________________________________________

"አያስፈልገኝም" ካሉ ለምን? ____________________

________________________________________

6. የሚያስተምሩበት የክፍለ ጊዜ ብዛት የስራ ጫና ፈጥሮብዎታል?

ሀ. አዎን ፈጥሮብኛል ለ. አልፈጠረብኝም

7. የማስተማር ተግባርዎን የሚያከናውኑት ግለመር /self-contained/ በሆነው የማስተማር ዘዴ ነው?

ሀ. አዎ ለ. አይደለም

8. በተራ ቁጥር "7" ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ ዘዴው ለመማር ማስተማሩ ሂደት ያለው ጠቀሜታ ምን ሆኖ አግኝተውታል?

ሀ. አሉታዊ ለ. አዎንታዊ

"አሉታዊ" ካሉ ለምን? ____________________________________________

________________________________________________________________

"አዎንታዊ" ካሉ ለምን? ___________________________________________

________________________________________________________________

9. በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሚገኘው የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የ4ኛ ክፍልን የአማርኛ ትምህርት ለማስተማር ተስማሚ የሆኑትን መሳሪያዎች ያዘጋጀው በምን ያህል ደረጃ ነው?

ሀ. በበቂ ሁኔታ ለ. በጥቂቱ

ሐ. ፈጽሞ አላዘጋጀም መ. ት/ቤቱ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የለውም

10. በየክፍሉ የሚገኙት ተማሪዎች ቁጥር መብዛት በ4ኛ ክፍል የአማርኛ መርሀ ትምህርት ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አስከትሏል?

ሀ. አዎን ለ. አላስከተለም

11. በተራ ቁጥር "10" ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያጋጠሙዎትን ችግሮች ባጭሩ ይግለፁ።

________________________________________________________________

________________________________________________________________

____________________

12. በትምህርት ቤትዎ የአማርኛ ቋንቋ ዲፓርትመንት አለ?

ሀ. አዎን ለ. የለም

13. ለ4ኛ ክፍል የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ፡-

ሀ. በጣም ውስብስብ ነው ለ. በመጠነኛ ሁኔታ ውስብስብ ነው

ሐ መካከለኛ ነው መ. በጣም ቀላል ነው

14. በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ የተመለከቱት ይዘቶች በሙሉ በመምህሩ መምሪያ ላይ በተሟላ አኳኋን ተብራርተዋል?

ሀ. አዎን ለ. በበቂ ሁኔታ አልተብራሩም

15. የተማሪውን መማሪያ መጽሀፍ እንደዋንኛ የማስተማሪያ መሳሪያ አድርገው ሁልጊዜ ይጠቀሙበታል?

ሀ. አዎን ለ. ሁልጊዜ አልጠቀምም

16. ብዙውን ጊዜ ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ሌላ ተጨማሪ የማጣቀሻ መጻህፍት ይጠቀማሉ?

ሀ. ማግኘት ስለማልችል አልጠቀምም

ለ. የተማሪው መጽሀፍ ራሱ በቂ ስለሆነ ሌላ አልጠቀምም

ሐ. የተለያዩ መጻህፍት እጠቀማለሁ

17. በተማሪው መጽሀፍ ውስጥ ከቀረቡት መልመጃዎች በተጨማሪ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ሊያዳብሩ የሚችሉ ክንውኖች /tasks/ አዘጋጅተው ክፍል ውስጥ ያቀርባሉ?

ሀ. የለም አላቀርብም ለ. አልፎ አልፎ አቀርባለሁ ሐ. ብዙ ጊዜ አቀርባለሁ

18. በትምህርት ቤትዎ ውስጥ ባሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የስራ ልምድን የመለዋወጥና በስራ የመረዳዳት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ልማድ አለ?

ሀ. አዎን አለ ለ. የለም

19. በተራ ቁጥር "18" ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ በምን መልኩ እንደሆነ በአጭሩ ይግለጹ።

____________________________________________

____________________________________________

____________________________________________

20. በተራ ቁጥር "18" ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "የለም" የሚል ከሆነ ምክንያቱን ባጭሩ ያብራሩ።

______________________________________________

______________________________________________

21. አሁን ያለው የትምህርት ቤትዎ አደረጃጀት በመርሃትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ብለው ያምናሉ?

ሀ. አዎን አምናለሁ ለ. በከፊል አምናለሁ ሐ. አላምንም

22. ከአዲሱ ስርዓተትምህርት አንጻር ስላሉት የስራ ድርሻ፥ ሀላፊነትና ግዴታ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ አለዎት?

ሀ. አዎን አለኝ ለ. በመጠኑ አለኝ ሐ. የለኝም

23. ከአዲሱ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት ጋር በተለያዩ አውደ ጥናቶች ወይንም በሌላ መንገድ ትውውቅ አድርገዋል?

ሀ. አዎን ለ. አላደረግሁም

24. የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩት

ሀ. በፍላጎት ነው ለ. ያለፍላጎት በመመደብ ነው

25. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርት በመተግበር ሂደት ላይ ያጋጠሙዎት ዋና ዋና ችግሮች ምንድን ናቸው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

26. የአማርኛ ቋንቋ መርሃትምህርትን አተገባበር በተመለከተ የትምህርት ቤቱ ርዕሠ መምህር ከእርስዎ ጋር በግል ወይንም በዲፓርትመንት አማካኝነት ምን ያህል ውይይት ያደርጋሉ?

ሀ. ብዙ ጊዜ ለ. አልፎ አልፎ ሐ. ፈጽሞ አያደርግም

ለ. ትምህርት ቤቱ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎችን በምን ያህል ደረጃ እንደሚያሟላ ለማመልከት ከዚህ በታች በሰንጠረዡ ውስጥ ከቀረቡት ሶስት አማራጮች ውስጥ ትክክል ነው የሚሉትን በመምረጥና ይህን የእርማት ምልክት / ✓ / በማድረግ ይጠቁሙ።

| ተ.ቁ | ለመማር ማስተማር የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በበቂ ሁኔታ | ባልተሟላ ሁኔታ | ፈጽሞ አይስተዋም |
| 1 | የትምህርት እቅድ /Lesson Plan/ ማዘጋጃ ደብተር/ ወረቀት | | | |
| 2 | እስኪርቢቶዎችና እርሳሶች | | | |
| 3 | ለቴስት ማዘጋጃ የሚሆን ወረቀት | | | |
| 4 | ለማስታወሻ መያዣ የሚሆን ወረቀት | | | |
| 5 | ለተከታታይ ምዘናዎች ውጤት መመዝገቢያ የሚሆን ቅጽ /ፎርም/ | | | |
| 6 | ልዩ ልዩ መርጃ መሳሪያዎች | | | |

## ክፍል አራት

ከዚህ በታች በተተወው ባዶ ስፍራ በመርህትምህርቱ ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራሉ የሚሏቸውን ነገሮች ወይም ሁኔታዎች /ካሉ/ በዝርዝር ይግለጹ።

________________________________________

## ክፍል አምስት

እታች በሰንጠረዥ ውስጥ የሰፈሩት ዝርዝር ሀሳቦች በ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ትግበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው:: ከእርስዎ የመማር ማስተማር ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የተጽኖአቸውን መጠን በቅደም ተከተል በመፈረጅ /ከ1-12 ተራ ቁጥር በመስጠት/ ይጠቁሙ::

ማስታወሻ:- የደረጃ ተራ ቁጥሩን የሚጽፉት "የተጽኖው ደረጃ" በሚለው ስር ባሉት ባዶ ቦታዎች ውስጥ ነው::

| ተ.ቁ | በትግበራው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች | የተፅእኖው ደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | ማስተማሪያ መሳሪያዎች/መርሀትምህርት፣ የመምህር መምሪያ፣ ወዘተ/ እጥረት | |
| 2 | የተማሪው መጻህፍት እጥረት | |
| 3 | ከትምህርት ቤቱ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚደረግ ድጋፍ ማነስ ወይም የመርጃ መሳሪያዎች አለመኖር | |
| 4 | በመርሀትምህርቱ ውስጥ የሰፈሩት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የእውቀት ደረጃ ጋር አለመመጣጠን /የትምህርቱ ከባድነት/ | |
| 5 | በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ቁጥር ብዛት | |
| 6 | ከተለያዩ አስተዳደራዊ ክፍሎች ለመምህራን የሚደረግ ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን | |
| 7 | አዲሱን መርሃትምህርት አስመልክቶ ለመምህራን የተሰጠ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና አለመኖር | |
| 8 | የክፍሉ ውስጣዊ ገፅታ /የስሌዳው ጥራት፣ የዴስኮች አቀማመጥ፣ ወዘተ/ አመቺ አለመሆን | |
| 9 | በመምህራን ላይ የሚኖር የስራ ጫና | |
| 10 | የማስተማሪያ ስነ ዘዴው ግልፅ አለመሆን | |
| 11 | መምህራን በአዲሱ መርሃትምህርት መሰረት አማርኛ ቋንቋ ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን | |
| 12 | የተማሪዎቹ ቀደምት ችሎታ (Background Knowledge) እናሳ መሆን | |

አባሪ ሐ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ**

**መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና**

**ስነ ጽሁፍ ክፍል /TEAM/**

**<u>ከትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን የሚሰበሰብ መረጃ</u>**

<u>የተከበሩ ርዕሰ መምህር:</u>

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በአሁኑ ጊዜ እየተሰራበት ያለው የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት /Syllabus/ ከአፈጻጸም ወይም ከአተገባበር አኳያ ምን መልክ እንዳለው መረጃ መሰብሰብ ብቻ ነው። ከመጠይቁ የሚገኘው መረጃ ለዚሁ ጥናት ብቻ የሚውል ይሆናል። ስለዚህ ለጥናቱ ውጤታማነት የእርስዎን በግልጽነት የተሞላ እውነተኛ ምላሽ አጥኚው በትህትና ይጠይቃል። ስለመልካም ትብብርዎ በቅድሚያ ምስጋና ይድረስዎ።

<u>መመሪያ</u>: ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽዎን ይህን የእርማት ምልክት /✓/ በማድረግ፣ ወይም የምላሽዎን የምርጫ ፊደል በማክበብ እንዲሁም የጽሁፍ ምላሽ ለሚፈልጉት ደግሞ የተሟላ መልስ በመጻፍ ይግለጹ።

1. የትምህርት ቤቱ ስም ______________ ዞን ________ ወረዳ ______
2. ዕድሜ /የእርስዎ / ________
3. የትምህርት ደረጃ __________
4. በርዕሰ መምህርነት ያገለገሉበት ዓመት ብዛት ______________
5. በትምህርት ቤትዎ የሚገኙ መምህራን ብዛት: ወንድ ______ ሴት ______
6. የመምህራኑ ብዛት ከስልጠናቸው አኳያ ሲገለጽ፦
   - የኮሌጅ ዲፕሎማ ______
   - 12 + 1 ______
   - 12 + 2 ______
   - 12 + TTI ______
   - 10 + 2 ______
   - 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁና ሌላ ስልጠና የሌላቸው ________
7. በትምህርት ቤትዎ ያሉ የመማሪያ ክፍሎች ስንት ናቸው? ________
8. በትምህርት ቤትዎ ውስጥ በአንድ ክፍል በአማካይ ስንት ተማሪዎች ይገኛሉ? ______

9. በትምህርት ቤትዎ ውስጥ በአንድ ክፍል በአማካይ ስንት የተማሪ መቀመጫዎች ይገኛሉ? __________

10. በትምህርት ቤትዎ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ይገኛል?

አዎን ______ የለም ______

11. በትምህርት ቤትዎ ቤተመጻህፍት ይገኛል?

አዎን ______ የለም ______

12. በትምህርት ቤትዎ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ እጥረት አለ?

አዎን አጥረት አለ __________ እጥረት የለም __________

13. በትምህርት ቤትዎ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት /syllabus/ አለ?

አለ ________ የለም ________

14. ትምህርት ቤትዎ የተማሪው መጻህፍት በትክክል ይደርሱታል?

አዎን ________ በትክክለኛ ጊዜ አይደርሱትም ________

15. በተራ ቁጥር "14" ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "በትክክለኛ ጊዜ አይደርሱትም" የሚል ከሆነ ምክንያቱ ምንድን ነው?

ሀ. የበጀት ችግር

ለ. ሀላፊነቱን የሚወጣ ሰው አለመኖር

ሐ. ሌላ ካለ ይጠቀሱ ____________________________________________

16. በትምህርት ቤትዎ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎችና የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ምጥጥን /Ratio/ ምን ያህል ነው?

ሀ. 1:1 /አንድ መጽሀፍ ለአንድ ተማሪ/

ለ. 1:2

ሐ. 1:3

መ. 1:4

ሠ. 1:5

ረ. አንድን መጽሀፍ ከአምስት ተማሪዎች በላይ ይጋሩታል

ሰ. ምንም የለም/ተማሪው ራሱ ገዝቶ እንዲጠቀም ይገደዳል/

17. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በማስተማር ላይ እያሉ እክፍላቸው ገብተው ምልከታ አድርገው ያውቃሉ?

ሀ. አዎን አውቃለሁ ለ. አድርጊ አላውቅም

18. በተራ ቁጥር "17" ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን አውቃለሁ" የሚል ከሆነ በክፍለ ጊዜው የተመለከቷቸው ከመማር ማስተማሩ ሂደት ጋር የተያያዙ ዋና ዋና ችግሮች/ካሉ/ ምን ምን ናቸው? ______________________

______________________

______________________

19. ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በተናጠል ወይም በዲፓርትመንት ስብሰባ አማካኝነት የቋንቋውን መማር ማስተማር ሂደት አስመልክቶ ውይይት አድርገው ያውቃሉ?

ሀ. አዎን ለ. አላውቅም

20. በተራ ቁጥር "19" ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ ብዙውን ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተናጠል ወይም በዲፓርትመንት ውይይታቸው ወቅት የሚያነሷቸው ከመርሀትምህርቱ አተገባበር ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

______________________

______________________

______________________

21. በትምህርት ቤትዎ ያሉ የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አዲሱን መርሀትምህርት በሚገባ ለተመገበር ተጨማሪ ስልጠና ያስፈልጋቸዋል ብለው ያምናሉ?

ሀ. አዎን አምናለሁ ለ. አላምንም

ምክንያትዎን ባጭሩ ይግለጹ ______________________

______________________

______________________

22. ለትምህርት ቤትዎ የተመደበ በጀት አለ?

ሀ. አዎን ለ. የለም

23. በተራ ቁጥር 22 ስር ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ በጀቱ በቂ ነው ብለው ያምናሉ ወይስ በቂ አይደለም? አስተያየትዎን ይስጡ።

______________________

______________________

24. ከወረዳው ወይም ከዞኑ የትምህርት ጽህፈት ቤት አዲሱን ስርዓተትምህርት ለመተግበር ለትምህርት ቤትዎ የሚደረግለት ድጋፍ ምን ያህል ነው?

ሀ. በቂ ነው ለ. በቂ አይደለም ሐ. ምንም የለም

25. ትምህርት ቤትዎ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱትን ተፈላጊ የመማሪያ/ማስተማሪያ ቁሳቁስ ለመምህራኑ በምን ያህል ደረጃ ሊያቀርብ እንደሚችል ለማመልከት ይህን የእርማት ምልክት /✓/ በማድረግ ምላሽዎን ይስጡ።

| ተፈላጊ ቁሳቁስ | በበቂ ሁኔታ ያቀርባል | በቂ ባልሆን መልኩ ያቀርባል | ፈጽሞ አያቀርብም |
|---|---|---|---|
| የትምህርት ዕቅድ ማዘጋጃ ደብተሮች | | | |
| እስኪርቢቶና እርሳስ | | | |
| የተከታታይ ምዘናዎች ውጤት መመዝገቢያ ቅጾች | | | |
| ለመምህራን ማስታወሻ /ኖት/ ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| የቴስት ማዘጋጃ ወረቀት | | | |
| ልዩ ልዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች /ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን/ | | | |

26. የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀትምህርት /syllabus/ አተገባበር በሚመለከት በትምህርት ቤትዎ ያጋጠሙ ችግሮች ካሉ በዝርዝር ይጥቀሱ፣

አባሪ መ

የክፍል ምልከታ ለማካሄድ የሚረዳ

እርከናዊ ልኬት (Rating scale)

የትምህርት ቤቱ ስም ____________________

ዞን ________________ ወረዳ ____________

ክፍል ______________

ምልከታው የተካሄደበት ቀን ______________ ሰዓት __________

ክፍለ ጊዜ ____________________

የእለቱ ትምህርት ርዕስ ____________________

| ተ.ቁ | የማስተማር ክንውን | በተደጋጋሚ | አልፎ አልፎ | አያደርገም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የእለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ባለፈው ክፍለ ጊዜ የተማሩትን ተማሪዎቹ እንዲያስታውሱ ያበረታታል /ታበረታታለች (ክለሳ ያደርጋል /ታደርጋለች) | | | |
| 2 | የእለቱን ትምህርት ግልጽ በሆነ መንገድ ያስተዋውቃል /ታስተዋውቃለች | | | |
| 3 | የትምህርቱን ዓላማ ይገልጻል/ትገልጻለች | | | |
| 4 | ተማሪዎች ተግባራትን/Tasks/ በቡድን እንዲሰሩ ያደርጋል /ታደርጋለች | | | |
| 5 | የቡድን ስራውን እየተዘዋወረ ይቆጣጠራል /ትቆጣጠራለች | | | |
| 6 | መርሃ ትምህርቱን መሰረት ያደረጉ ተግባራት በክፍል ውስጥ እንዲከናወኑ ለተማሪዎች ይሰጣል/ትሰጣለች | | | |
| 7 | ተግባራት እንዴት መከናወን እንዳለባቸው ግልጽ የሆነ መግለጫ ለተማሪዎች ይሰጣል/ትሰጣለች | | | |
| 8 | ለእያንዳንዱ ይዘት የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ይጠቀማል/ትጠቀማለች | | | |
| 9 | ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያበረታታል (ባጫጭር ጥያቄና መልስ የአልተገደበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ተማሪዎችን ያበረታታል /ታበረታታለች/ | | | |
| 10 | ጠቃሚ ነጥቦችን በሰሌዳ ላይ ይጽፋል/ትጽፋለች | | | |
| 11 | ምጋቤ ምላሽ (feed back) ከተማሪዎች ይጠይቃል/ትጠይቃለች | | | |
| 12 | በቂ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች | | | |
| 13 | የተማሪዎችን የቤት ስራም ሆነ የክፍል ስራ በማረም ይቆጣጠራል/ትቆጣጠራለች | | | |
| 14 | የመማር ማስተማሩን ሂደት ተማሪመራሽ (Student center) ለማድረግ ይጥራል/ትጥራለች | | | |
| 15 | የእለቱን ትምህርት አስመልክቶ ማጠቃለያ ይሰጣል /ትሰጣለች | | | |

# አባሪ ሠ

እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ምን ያህል ዝርዝር አላማዎችና ምን ያህል ይዘቶች እንዳሉት እንዲሁም ምን ያህል ክፍለ ጊዜ እንደተመደበለትና በፈተናው ውስጥም በየትኞቹ ተራ ቁጥሮች እንደተገለጸ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የትምህርት ክፍል | የ ዝ ር ዝ ር አ ላ ማ ዎ ች ብዛት | የይዘት ብዛት | የተሰጠው ክፍለ ጊዜ ብዛት | የጥያቄዎች ተራ ቁጥር (በፈተናው ላይ) |
|---|---|---|---|---|
| ማንበብና ማስተዋል | 3 | 3 | 7 | ሀ. ከ 1-5<br>ለ. 9፡10፡11፡17 |
| ጽህፈት | 8 | 8 | 16 | ለ. 1፡2፡4፡5<br>ሐ.<br>ሠ. 1፡5 |
| ስነልሳን | 8 | 8 | 37 | ለ.3፡6፡7፡8፡12፡13፡<br>14፡15፡16፡18፡19<br>መ. 1፡2<br>ሠ. 2፡3፡4 |
| ድምር | 19 | 19 | 60 | |

## አባሪ ረ

### ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

የትምህርት ቤቱ ስም ______________________ ኮድ __________

የተማሪው/ዋ ስም ________________________ ጾታ __________

ሀ. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ካነበብክ/ሽ በኋላ ከስሩ ያሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሺ.

### ሀውልቶች

በአገራችን ጥንታዊና ዘመናዊ የሆኑ ሐውልቶች አሉ፡፡ ጥንታዊ የሆኑት ሀውልቶች የተሰሩት በድንጋይ ወይም በአለት ነው፡፡ ከነኚህም መካከል በትግራይ ክልል የሚገኙትን የአክሱም ሀውልቶች በዋና ምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከዘመናዊ ሀውልቶች መካከል በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የምኒሊክ ሐውልት፥ የነጻነት ሐውልት፣ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት፣ የየካቲት 12 አደባባይ ሐውልትና የይሁዳ አንበሳ ሐውልት በዋና ዋና ምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የምኒልክ ሐውልት የአድዋ ድል አብሳሪና ድሉንም ላስገኙት ለዳግማዊ አፄ ምኒሊክ መታሰቢያነት የቆመ ነው፡፡ ሐውልቱ ሙሉ በሙሉ ከነሐስ የተሰራ ነው፡፡ የነጻነት ሐውልት ደግሞ በጣሊያን ወረራ ጊዜ አምስት ዓመት ሙሉ ለአገራቸውና ለህዝባቸው ነጻነት ሲሉ ለተፋለሙና ለወደቁ አባት አርበኞች መታሰቢያ ሆኖ የቆመ ነው፡፡ ይህ ሐውልት ከድንጋይ የተሰራ ሲሆን በዙሪያው ልዩ ልዩ ምስሎች ተቀርጸውበታል፡፡ የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት የተሰራው ሙሉ በሙሉ በእብነ በረድ ሲሆን መታሰቢያነቱም ፋሽስቶች በግፍ ለገደሏቸው ጳጳስ ለአቡነ ጴጥሮስ ነው፡፡ የተገደሉትም አገራችን በፋሽስት ኢጣሊያ በተወረረችበት ወቅት የኢትዮጵያን ህዝብ ለትግል ይቀሰቅሱ ስለነበረ ነው፡፡

የየካቲት 12 አደባባይ ሐውልት ደግሞ ስድስት ቅርጻቅርጽ በአንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ሲሆን የተሰራውም ከነሀስ ነው፡፡ በላዩ ላይ ያሉት ቅርጻቅርጽ የሚያንጸባርቁት የፋሽስት ጣሊያንን ጭፍጨፋ ነው፡፡ ማለትም ወራሪዎች በህዝባችን ላይ ያደረሱትን በደል ያሳያል፡፡ በመሆኑም በታሪክ መዘክርነቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

/በደቡብ ክልል ከተዘጋጀው የአራተኛ ክፍል የአማርኛ
መማሪያ መጽሀፍ የተወሰደ/

1. በምንባቡ መሰረት ጥንታዊ ሐውልቶች የተሰሩት ከምንድን ነው?

ሀ. ከብረት　　ሐ. ከእለት

ለ. ከሸክላ　　መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ በምንባቡ መሠረት ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የምኒሊክ ሐውልት በዘመናዊ ሐውልቶች ውስጥ የሚካተት ሲሆን የተሰራውም ከነሀስ ነው

ለ. የነፃነት ሐውልት የተሰራው ከድንጋይ ስለሆነ ጥንታዊ ሐውልት ነው

ሐ. የአቡነ ጴጥሮስ ሐውልት ሙሉ በሙሉ የተሰራው ከነሐስ ነው

መ. ሁሉም ትክክል ነው

3. የነጻነት ሐውልት የተሰራው ለምን መታሰቢያ ተብሎ ነው?

ሀ. ጣሊያን ለጨፈጨፋቸው የአዲስ አበባ ህዝቦች

ለ. ለአባት አርበኞች

ሐ. ለሀገራችን ነፃነት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

4. ፋሽስቶች አቡነ ጴጥሮስን የገደሏቸው ለምንድን ነው?

ሀ. ሲዋጉ አግኝተዋቸው

ለ. ሀይማኖታቸውን አልቀይርም ስላሉ

ሐ. የሀገራችንን ህዝብ ለትግል ስለቀሰቀሱ

መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

5. የየካቲት 12 አደባባይ ሐውልት ላይ ያሉት ቅርጻቅርጽ ምን ያሳያሉ?

ሀ. የፋሽስት ኢጣሊያን ጭፍጨፋ

ለ. የጀግኖቻችንን አኩሪ ገድል

ሐ. ወራሪዎች በህዝባችን ላይ ያደረሱትን በደል

መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከስራቸው ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥና የምርጫውን ፊደል በማክበብ መልስ ስጥ/ጪ፡፡

1. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ ጭረት / - / የሚቀበል ነው፡፡

ሀ. ወታደር ለ. ቤተመጻህፍት ሐ. ብረትምጣድ መ. ለ እና ሐ

2. "ቃል" እና "መጠይቅ" የሚሉት ሁለት ቃላት በጭረት ሲያያዙ ______ የሚል ጥምር ቃል ይሰጣሉ፡፡

ሀ. ቃል-መጠየቅ ለ.ቃለ-መጠይቅ ሐ. የመጠይቅ-ቃል መ. የቃልመጠይቅ

3. "ወይዘሮ" የሚለው ቃል በምህጻረ ቃል ሲገለጽ ____ ይሆናል፡፡

ሀ. ወ.ይ ለ. ወ.ሮ ሐ. ወይ.ሮ መ. ወ.ዘ

4. ከሚከተሉት አማራጭ አረፍተ ነገሮች መካከል ትክክለኛ የትእምርተ ጥቅስ አጠቃቀም ያልያዘው የቱ ነው?

ሀ. "ንጽህናችሁን መጠበቅ አለባችሁ፡፡" በማለት የሳይንስ አስተማሪያችን የተናገሩት ትዝ አለኝ፡፡

ለ. "ፀጉሩን እያሻሹ ተማር በርታ" ልጄ፡፡ አሉና መከሩት፡፡

ሐ. በጣም ስለደከመው "ከአንድ ሰዓት በኋላ ቀስቅሱኝ፡፡" ብሎ ተኛ፡፡

መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡

5. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል ትእምርተ ጥቅስ /" "/ የሚያስፈልገው የቱ ነው?

ሀ. ብዙ ከመናገር ብዙ ማዳመጥ ይመረጣል ሲባል እንሰማለን፡፡

ለ. የተማረ ሰው ይግደለኝ፡፡ ብላ ዝም አለች፡፡

ሐ. አስቴር የቀበሌያችን ጽህፈት ቤት ሰራተኛ ነች እንዴ?

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

6. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ድርብ ቃል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግንደቆርቁር ለ. ቅብጥብጥ

ሐ. ቅጠላቅጠል መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

7. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ድርብ ቃል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ልበቢስ ለ.ብረትምጣድ ሐ.አረፍተነገር መ.መልሱ አልተሰጠም

8. "ቤት" የሚለው ቃል ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የቱን ሊያካትት ይችላል?

ሀ. ጎጆ ለ. ቪላ ሐ. ፎቅ መ. ሁሉንም ያካትታል

9. "ተፈተነ፥ተፈተነች፥መፈተን፥አፈታተን" የሚሉ ቃላት በመዝገበቃላት ውስጥ

በ________የፊደል ተራ ይገኛሉ።

ሀ. "ተ" ለ. "ፈ" ሐ. "መ" መ. "አ"

10. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በትክክለኛ የፊደል ተራ ቅደም ተከተል የተሰለፉ ቃላት የያዘው የቱ ነው?

ሀ. ኢትዮጵያ፥ ሱዳን፥ ሊቢያ፥ ሞሮኮ፥ ናይጄሪያ

ለ. ቲማቲም፥ ሰላጣ፥ ካሮት፥ ሽንኩርት፥ ድንች

ሐ. መሰረት፥ ምስራቅ፥ ሙሉዓለም፥ ምህረት

መ. ቀለበት፥ ተራራ፥ ነፋስ፥ ጠረጴዛ

11. "በላ" ብሎ "ተመገበ" ካለ "ወደደ" ብሎ________ ይላል።

ሀ. ጠላ ለ. አፈቀረ ሐ. አልወደደም መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

12. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል የስም ገላጭ ያለበት የቱ ነው?

ሀ. ግርማ ኳስ ተጫዋች ነው

ለ. ጸዳለ ታታሪ ተማሪ ስለሆነች ጥሩ ውጤት አመጣች

ሐ. መማር አእምሮን ያሰፋል

መ. እኔ መኪና መንዳት እችላለሁ

13. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በመጥበቅና በመላላት ሁለት ፍቺ የሚሰጠው የቱ ነው?

ሀ. ክራር ለ. መሳል ሐ. አባይ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

14. "አየት" በሚለው ቃል ውስጥ በመጥበቅና በመላላት የፍቺ ለውጥ እንዲመጣ የሚያደርገው ፊደል የቱ ነው?

ሀ. "አ" ለ. "የ" ሐ. "ት" መ. "የ" እና "ት"

15. "ደብተሮች" በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ቅጥያ ________ ነው።

ሀ. "ሮች" ለ. "ች" ሐ. "ኦች" መ. ቅጥያ የለውም

16. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል መነሻና መድረሻ ቅጥያ ያለበት የቱ ነው?

ሀ. ስላየው ለ. እንጀመረ ሐ. ስለተመታን መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

17. "ደግ" ብሎ "ክፉ" ካለ "በልሀ" ብሎ ________ ይላል።

ሀ. ዘዴኛ ለ. ተንኮለኛ ሐ. ሞኝ መ. መሰርይ

18. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ሀረግ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ትልቅ ለ. በላ ሐ. ተጫወተ መ. እንደመጣ

19. ከሚከተሉት አረፍተነገሮች መካከል በቅርጹ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ምግብ በሰዓቱ መብላት በጣም ጥሩ ነው።

ለ. ደብተርህን ያዝና ወደ ክፍል ግባ!!

ሐ. አስቴር ዛሬ ትምህርት ቤት ለምን አልመጣችም?

መ. ሁሉም የተለያዩ ናቸው

ሐ. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በተገቢው ቅደም ተከተል አስተካክሏቸው።

የምታስተካክሏቸው ከ1-7 ተራ ቁጥር በባዶው ቦታ ላይ በመጻፍ ነው።

________ ሁለቱም አንድ ክፍል ውስጥ ይማራሉ።

________ አልማዝ የምትባል እህት አለችው።

________ በርትታ ስለምታጠናም ጥሩ ውጤት ታመጣለች።

________ ከበደ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነው።

________ አልማዝ ግን ከጨዋታ ይልቅ ትምህርቷን ትወዳለች።

________ ከበደ ከትምህርቱ ይልቅ ጨዋታ ይወዳል።

________ ስለዚህ ሁልጊዜ ትሸለማለች።

መ. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉት ቃላትና ሀረጎች የተዘበራረቁ ናቸው። በተገቢው ቅደም ተከተል ከተስተካከሉ የተሟላ አረፍተነገር ይመሰርታሉ። አስተካክሏቸውና አረፍተ ነገሮቹን እንደገና ጻፏቸው።

1. ተሰበረ የነበረው በጭንቅላቱ ሰውዬው ሸክላ ተሸክሞት ወድቆ።

________________________________________

2. እጃችሁን በፊት ከመብላታችሁ በሳሙና በውሀና ምግብ ታጠቡ።

________________________________________

ሠ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በትእዛዛቸው መሠረት መልስ ስጥ/ጪ።

1. የሚከተሉትን ሆሔያት በማገጣጠም እታች በቀረቡት ባዶ ቦታዎች ላይ አራት ቃላት ጻፍ/ፊ።

ሬ፡ጋ፡ና፡ተ

ሀ. ____________ ለ. ____________

ሐ. ____________ መ. ____________

2. "የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት" የሚለው ሀረግ በምህጻረ ቃል ሲገለጽ ____________ ይሆናል።

3. "ከበደ ገበያ ሔዶ ቀዳዳ ሱሪ ገዝቶ መጣ።" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጩ ____________ ነው።

4. "ያ ፖሊስ አንድ ሌባ ፊት ለፊት አይቶ ሮጠ" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙትን ሁለት ቃላት ቦታቸውን በመቀያየር ከበፊቱ የተለየ ትርጉም ያለው አረፍተ ነገር ጻፍ/ፊ።

________________________________________

5. ቀጥሎ የቀረቡትን ሁለት ቃላት መሰረት በማድረግ አምስትና ከዛ በላይ ቃላት ያላቸው አረፍተ ነገሮች ጻፍ/ፊ።

ሀ. ደነገጠ

ለ. ሾፌር

## አባሪ ሰ

### የካይ ስኩየር ($X^2$) ስታትስቲካዊ ስሌት

የመምህራኑን አመለካከት ለመመዘን ከቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ አሀዛዊ ውጤት

(60%)

የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉ 20 የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን

| ሴቶች | ወንዶች |
|---|---|
| 17 | 18 |
| 25 | 22 |
| 30 | 34 |
| 32 | 34 |
| 32 | 35 |
| 35 | 45 |
| 35 | 48 |
| 35 | |
| 43 | |
| 43 | |
| 47 | |
| 47 | |
| 53 | |

ከአጠቃላይ የመምህራኑ ውጤት የተገኘው አማካይ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | 18 | 22 | 25 | 30 | 32 | 32 | 34 | 34 | 35 |
| 35 | 35 | 35 | 43 | 43 | 45 | 47 | 47 | 48 | 53 |

$$\text{አማካይ} = \frac{710}{20}$$

$$= 35.5$$

1. በሰንጠረዥ 1 ውስጥ የሚገኘውን መረጃ ለመተንተን የቀረበ የ 'Chi-Square ($X^2$) ስሌት

$$x^2 = \frac{n\left[|AD - BC| - \frac{N}{2}\right]^2}{(A+B)(C+D)(A+C)(B+D)}$$

n = 20

A = 5 C = 8

B = 2 D = 5

$$x^2 = \frac{20\left[|25 - 16| - \frac{20}{2}\right]^2}{(5+2)(8+5)(5+8)(2+5)}$$

$$= \frac{20(9-10)^2}{7 x 13 x 13 x 7}$$

$$= \frac{20(1)}{8281}$$

$$x^2 = 0.002$$

2. በሰንጠረዥ 12 የቀረበውን መረጃ የተተነተነበት የ 'Chi-Square($X^2$)' ስታትስቲካዊ ስሌት

$$X^2 = \sum \frac{(f_O - f_e)^2}{f_e}$$

ማንበብና ማስተዋል

| Cell | $f_0$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $(f_o-f_e)^2/f_e$ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 13 | 14 | 1 | 0.071 |
| 2 | 16 | 14 | 4 | 0.286 |
| 3 | 12 | 14 | 4 | 0.286 |
| 4 | 11 | 14 | 9 | 0.643 |
| 5 | 18 | 14 | 16 | 1.143 |
| 6 | 14 | 14 | 0 | 0.000 |
| 7 | 23 | 22 | 1 | 0.045 |
| 8 | 20 | 22 | 4 | 0.182 |
| 9 | 24 | 22 | 4 | 0.182 |
| 10 | 25 | 22 | 9 | 0.409 |
| 11 | 18 | 22 | 16 | 0.727 |
| 12 | 22 | 22 | 0 | 0.000 |
| | | | | $X^2$=3.974 |

ጽህፈት

| Cell | $f_o$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $(f_o-f_e)^2/f_e$ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 17 | 11.5 | 30.25 | 2.630 |
| 2 | 10 | 11.5 | 2.25 | 0.196 |
| 3 | 11 | 11.5 | 0.25 | 0.022 |
| 4 | 12 | 11.5 | 0.25 | 0.022 |
| 5 | 10 | 11.5 | 2.25 | 0.196 |
| 6 | 9 | 11.5 | 6.25 | 0.543 |
| 7 | 19 | 24.5 | 30.25 | 1.235 |
| 8 | 26 | 24.5 | 2.25 | 0.092 |
| 9 | 25 | 24.5 | 0.25 | 0.010 |
| 10 | 24 | 24.5 | 0.25 | 0.010 |
| 11 | 26 | 24.5 | 2.25 | 0.092 |
| 12 | 27 | 24.5 | 6.25 | 0.255 |
| | | | | $X^2 = 5.303$ |

ስንልሳን

| Cell | $f_o$ | $f_e$ | $(f_o-f_e)^2$ | $(f_o-f_e)^2/f_e$ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 19 | 18 | 1 | 0.055 |
| 2 | 21 | 18 | 9 | 0.500 |
| 3 | 16 | 18 | 4 | 0.222 |
| 4 | 15 | 18 | 9 | 0.500 |
| 5 | 18 | 18 | 0 | 0.000 |
| 6 | 19 | 18 | 1 | 0.055 |
| 7 | 17 | 18 | 1 | 0.055 |
| 8 | 15 | 18 | 9 | 0.500 |
| 9 | 20 | 18 | 4 | 0.222 |
| 10 | 21 | 18 | 9 | 0.500 |
| 11 | 18 | 18 | 0 | 0.000 |
| 12 | 17 | 18 | 1 | 0.055 |
| | | | | $X^2=2.664$ |

degree of freedom (df) = (r-1) (k-1)

r = number of rows

k= number of columns

df = (2-1) (6-1)

= (1) (5)

= 5

So, the chi-square value at $p \leq 0.05$ significant level is 11.07

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የእኔ መሆኑንና ለጥናቱም የተጠቀምኩባቸውን ዋቢ ጽሁፎች በትክክል ማመልከቴን በፊርማዩ አረጋግጣለሁ።

ስም ዘለዓለም ወዳጅ

ፊርማ : ______

ቦታ፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

ቀን፡ 5/10/93 ዓ.ም